## ዘመነ፡ማርቆስ፡፲፱፻፸፬ ዓ፡ም

**መስከረም**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | | ፫ | ፲ | ፲፯* | ፳፬ |
| ሰ | | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ |
| ማ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ |
| ረ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ሐ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ዓ | ፩* | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ቅ | ፪* | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |

**ጥቅምት**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ሰ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ማ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ረ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| ሐ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |
| ዓ | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ | |
| ቅ | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ | |

**ኅዳር**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ሰ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ማ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ረ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ሐ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ዓ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| ቅ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |

**ታኅሣሥ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ |
| ሰ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ |
| ማ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ረ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ሐ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱* |
| ዓ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ቅ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |

**ጥር**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ሰ | | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ማ | | ፬ | ፲፩* | ፲፰ | ፳፭ | |
| ረ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |
| ሐ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ | |
| ዓ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ | |
| ቅ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ | |

**የካቲት**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ሰ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ማ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫* | ፴ |
| ረ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ሐ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| ዓ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |
| ቅ | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ | |

**መጋቢት**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ |
| ሰ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ማ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰* |
| ረ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ሐ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ዓ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ቅ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |

**ሚያዝያ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | | ፫ | ፲* | ፲፯ | ፳፬ |
| ሰ | | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ |
| ማ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ |
| ረ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ሐ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ዓ | ፩ | ፰* | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ቅ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫* | ፴ |

**ግንቦት**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ሰ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ማ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ረ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| ሐ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |
| ዓ | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ | |
| ቅ | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ | |

**ሰኔ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ሰ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ማ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ረ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ሐ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ዓ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| ቅ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |

**ሐምሌ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ |
| ሰ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ |
| ማ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ረ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ሐ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ዓ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ቅ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |

**ነሐሴ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እ | | ፪ | ፱ | ፲፮+ | ፳፫ | ፴ |
| ሰ | | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ማ | | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| ረ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |
| ሐ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ | |
| ዓ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ | |
| ቅ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ | |


**ጳጉሜን፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እ | ሰ | ማ | ረ | ሐ |
| ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ |

[illegible]

**እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደ ዘመነ ማርቆስ በሰላም አሸጋገራችሁ!**








ዋጋው ሃምሳ ሳንቲም ቁጥር 48 መስከረም ፲፱፻፸፬ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጥምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።

የ፲፱፻፸፬ ዓመተ ምሕረት በዐላትና አጽዋማት

| | | | |
|---|---|---|---|
| አበቅቴ | ፮ | ትንሣኤ ሚያዝያ | ፲ ቀን |
| መጥቅዕ | ፳፬ | ርክበ ካህናት ግንቦት | ፬ ቀን |
| ጾመ ነነዌ የካቲት | ፩ ቀን | ዕርገት ግንቦት | ፲፱ ቀን |
| በዐተ ጾም ዐቢይ የካቲት | ፲፭ ቀን | ጰራቅሊጦስ ግንቦት | ፳፱ ቀን |
| ደብረ ዘይት መጋቢት | ፲፪ ቀን | ጾመ ሐዋርያት ግንቦት | ፴ ቀን |
| ሆሣዕና ሚያዝያ | ፫ ቀን | ጾመ ድኅነት ሰኔ | ፪ ቀን |
| ስቅለት ሚያዝያ | ፰ ቀን | | |


አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም/አዘጋጅ ራደ አስረስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


## ማውጫ

አርእስት ገጽ


ደብዳቤዎች................................ ፩
በአዲስ ዓመት ለአዲስ ሥራ መዘጋጀት................................ ፪
የኒቅያ ጉባኤና ውጤቱ................................ ፫
ወጣቶች ከቡሄ እስከ መስቀል................................ ፬
ዜና ሊቃውንት................................ ፮
የድርሰት አጻጻፍ ዘዴ................................ ፯
የጌዴኦ ብሔረ ሰብእ ባህል................................ ፰
ምን እንርዳዎ?................................ ፲
የችቦና የደመራ መነሻ................................ ፲፪
የአክሱም ቅ ያሬድ ት ቤት................................ ፲፫
ሃይማኖትና ሥነ ምግባር................................ ፲፬
ስለ እውነት የሞተ................................ ፲፭
የተቀደሰ ጋብቻ................................ ፲፯
የትግራይ አብያተ ክርስቲያናት................................ ፲፰
የቤተሰብእ ዐምድ................................ ፳
ይህን ያውቁ ኖሯል?................................ ፳፩
ልማት በቤተ ክርስቲያን................................ ፳፫


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቁጥር 44 ግንቦት 1973 ዓ.ም. በወጣው መጽሔት በ16ኛው ገጽ ላይ የመቃብር ሃውልት ጥቅሙ ምንድነው?በሚል ርእስ የመቃብር ቤትን ሳይጨምር ጥያቄው የሐውልት ጥቅሙ ምንድነው ሲል ግልጽ የሆነ ጥያቄ ነበረ ። ምክንያቱም እኔ እንደመሰለኝ ለሟቹ በነፍስ በኩል ምን ጥቅም ይሰጣል ምሥጢሩን እንረዳው ማለት ነው እላለሁ ።

መልሱ ሲሰጥ በመቃብር ቤት በኩል ጥቅም ያለው መሆኑ ታውቆ ጥያቄ ያልቀረበበትን የማስረዳት መልስ የተሠጠበት ሆኖአል ።

ግን በሐውልቱ በኩል ሃውልት ያልተሠራላት የሙት ነፍስ ምንኩነኔ እንደሚጠብቃት ሃውልት የተሠራላት ነፍስ በንሥሃ የነጻ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚመራ ፈለግ መሆኑን ወይም ሟቹ በቁሙ ከአደረገው በጐአድራጎትና ትሩፋት በስተቀር ቋሚው በቀብሩ ላይ ሃውልት ቢሠራለት ለነፍሱ የሚሰጠው ጥቅም እንደሌለው ከ2ቱ አበይት አንድ መልስ ሳይሰጥበትና እንዲያውምንስሐ ገብተን ኃጢአታችንን ታጥበን የሞትን ለመሆኑ ሳይታወቅ በቁማችን ሳንፋቀር በሞተ ጊዜ ወገኑ ተበድሮ ወይም ሟቹ ከበጐ ሥራ ላይ ሣያውለው ወገኑን ሣያጠግብበት በስስት ያኖረውንገንዘብ ለሃውልት በሚያረገው ወጭና ድካም ሁሉ እየተገረምን ሳለን በአሁኑ መልስ ላይ የወጭ መጨመሪያ ቁሳቁስና ዘበኛ እንዲቋቋምለት ጠቁመዋል ። እንግዲህ የሐሳቡ ደጋፊ ወይም የተቀዋሚነት ነጥብ ከማዝነባችን በፊት በቀብር ላይ የሐውልት መቀረፅ በእግዚአብሔር በኩል አስታራቂነቱየቱንያህልእንደሆነወይም ተቀባይነት የሌለው ድካም እንደሆነ የግዕዝ ሚስጥሩ ተተረጉሞ እንዲገለጽልን እየተማፀንን መልሱን እንጠባበቃለን ።

አቶ መኰንን ጋሻነህ

አቶ መኰንን ጋሻነህ የሐውልት ጥቅሙ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ ደርሶን ተመልክተነዋል ። አንድ በአንድ አንብበው ስለጠየቁ በጣም አመሰግናለሁ።ስለሐውልትጥቅም፣መቼ እንደተጀመረና ከተሠራም በኋላ የሚጠቅመው ለቋሚ ዘመዶቹ ማስታወሻ እንዲሆን እንጂ ለሟቹ በነፍስ የሚረባው ምንም ጥቅም የለም ። ቀጥሎም በሟቹ ስም ብዙ ገንዘብ አውጥተው ሐውልት ካሠሩ በኋላ የሐውልቱ ቁሳቁስ በሌቦች ስለሚሰረቅና ጠባቂም ባለመኖሩ ስለሚፈራርስ ዕዳትም ስለሚያጣ የሚሠራው ሐውልት ጥቅሙ ምንድነው? ሠሪዎቹ ከገንዘባቸውም ሳይሆኑ ከሐውልቱም ሳይሆኑ ቀሩ ለማለት እንጂ የሞተውን ሰው በነፍስ ይጠቅመዋል ለማለት አይደለም ። እርስዎ እንዳሉት ሰው የሚጸድቀው በቁሙ በሠራው መልካም ሥራ ካልሆነ በቀር ሐውልት ቢሠራለት ባይሠራለት ነፍሱን ከኩነኔ ወይም ከወቀሳ ሊያድናት አይችልም ።

አቶ መኰንን ጋሻነህ እንዳሉት ሟቹ በቁመናው ሳለ በገንዘቡ ወገኑን ሳይጠቅምበት በበጐ ሥራ ላይ ሳያውለው እርሱ በስስት ያኖረውን ገንዘብ ወይም ዘመዶቹ ተበድረው ሐውልት ቢያሠሩለት ለቋሚዎቹ ካልሆነ በቀር ለሟቹ መታሰቢያ እንጂ ለነፍሱ ጥቅም አይሆነውም ። ለሙቱ የሚጠቅመው ግን በቁመናው ሳለ የሠራው ሥራ ብቻ ነው ። እንግዲህ ለማንኛውም ሰው ሐውልት ማሠራት ጠቃሚ አለመሆኑ ኢሳይያስ እንዲህ ብሎታል' መቃብር በዚህ ያስወቀርህ ከፍ ባለው ሥፍራ መቃብር ያሠራህ በዚህ ምን አለህ? በዚህስ በአንተ ዘንድ ማን አለ? እነሆ እግዚአብሔር በኃይል ወርውሮ ይጥልሃል አጠንክሮም ይጨብጥሃል ኢሳ 22፥16 ።

ክርስቶስም በሚያስተምርበት ጊዜ "እናንተ ግብዞች ጻፎች ፈሪሳውያን በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጡ ግን የሙታን አጥንት ርኩስትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ" ሲል ሐውልት ጠቃሚ አለመሆኑን ተናግሮአል ማቴ ም.24.ቁ.26 ።

እንግዲህ አቶ መኰንን ሊረዱልኝ የምፈልገው ቢኖር የሐውልት ጥቅሙ ምንድነው? ተብሎ የተጻፈው ሐውልቱን የሠሩት ሰዎች ሟች ዘመዳቸውን ለማስታወስእንጂእርስዎእንዳሉትሟቹ በሐውልቱ መሠራት ይጠቀማል ለማለት አይደለም ።

•••

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅድሚያ በእግዚአብሔር ስም ሰላምታ አቀርባለሁ ከመጽሔታችሁ ቁጥር 41 ና 42 ያልደረሰኝ ስለሆነ በምን እንደቀረ ለመረዳት ጠይቄ ነበር ግን መልስ አልተሰጠኝም ስለዚህ መልስ ያልተሰጠኝ በምን ምክንያት ነው?

2ኛ/ በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትውለድ እምወለተ ወለትከ ወወእድህክ ውስተ መርህብከ ወእተቤዘወከ በመስቀልየ ያለው ቀሌምንጦስ ነው ጌታ ከተወለደ በኋላ እንዴት ሊጸፍ ቻለ ?

3ኛ/ በስሌን መቀበር መች ተጀመረ በየት ሀገር ነው ?

ዲ/ ኃይሉ ወ/ሥላሴ

ዲያቆን ኃይሉ ወልደ ሥላሴ ስላቀረቧቸው ጥያቄዎች እናመሰግናለን ነገር ግን ካቀረቧቸው ብዙ ጥያቄዎች አስፈላጊዎች ለሆኑት ብቻ መልስ ሰጥተናል።

1ኛ/ ከመጽሔታችን ቁጥር 41ና 42 ያልደረሰዎት መሆኑን ገልጸዋል ነገርግን የጠየቋቸው መጽሔቶች በማከፋፈያ ኮሚቴ በኩል የተላኩ መሆናቸውን ስላ

ወደ ፫ኛው ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# በአዲስ አመት ለአዲስ ሥራ መዘጋጀት

አያሌ ዓመታት አልፈዋል ። አሁንም ያልፋሉ ፣ ነገር ግን ''ጊዜ ራሱን አይደግምም'' እንደተባለው ሁሉ ያለፉት ጊዜያት ተመልሰው አይገኙም ሌላው አዲስ ዓመት ቢመጣ እንጂ ። መሽቶ ሲነጋ አዲስ ዕለት ፣ አንዱ ወር አልፎ ሌላው ሲብት አዲስ ወር የነበረው ዓመት ተፈጽሞ የሚከተለው ሲገባ አዲስ ዓመት ይባላል ።

ስለዚህም ''እግዚአብሔር ለሰው ከሰጠው ሀብት የማያረጅና የማያፈጅ ጊዜ ብቻ ነው'' ሲሉ ብዙ ሊቃውንት ተናግረዋል ። ሥራን ለማከናወን አስፈላጊ ከሆኑት ዋና ዋና መሣሪያዎች አንደኛው ጊዜ ነው ጊዜ ሲባልም ሰዓታትን ፣ ዕለታትን ፣ ወራትንና ዓመታትን ያጠቃልላል ።

በምድር ላይ ለሰው ምንም ቢኖረው ከጊዜ የበለጠ ውድ ነገር አይኖርም ይኸውም ደቂቃን በደቂ ሰዓትን በሰዓት ዕለትን በዕለት ተቆጣጥሮ በመልካምና በጠቃሚ ሥራ ያሳለፈ እንደሆነ ነው ። የጊዜ ባለቤት እግዚአብሔር ጊዜን የሰጠ ሰዎች ሠርተው ሊጠቀሙበት በሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ሥራ ሠርተው የማያልፍ ስም ሊቀዳጁበት ነው እንጂ እንዲሁ ቁጭ ብለው ሲመሽና ሲነጋ ሊመለከቱት አይደለም ። አጭር ውድና ፈጣን የሆነውን ጊዜ ያለ ሥራ ማሳለፍ ተገቢ አይደለም ።

ጊዜና ሥራ ርምጃን ይለውጣል ። ወደኋላ መለስ ብሎ ያለፉትን ዓመታት ታሪክ የሚመረምርና የሚያስተውል ብልህ ካለ ጊዜ ብዙ ሰዎች ን በሥራ ሲጥል ጥቂቶችን ደግሞ በሥራ አንስቶአል ። ጊዜ የሚሠሩበትን ያከብራል በከንቱ የሚያሳልፉትንም ያዋርዳል ።

የሚመጣው ጊዜ አዲስ ቢሆንም አጭርና ውድ ነው ሰዎች ህልውናቸውን የሚያሳውቁበት ጊዜና ሥራ ነው በከንቱ ያለፈ ጊዜ ተመልሶ ሊገኝ አይችልም ። የሰው ልጅ ከአጣቸው በኋላ መልሶ ሊያገኛቸው የሚችል ነገሮች አሉ ።

ለምሳሌ የጤና ጉድለት ቢደርስ በሐኪም እርዳታ በልዩ ልዩ መድኃኒትና በእግዚአብሔር አዳኝነት የተጓደለውን ጤንነት ማስተካከልና ጤናማ መሆን ይቻላል ገንዘብ ቢጠፋ በርትቶ በመሥራት የጠፋውን ገንዘብ መተካት ይቻላል ። ያለ ሥራ በከንቱ የጠፋ ጊዜ ግን ለጸጸትና ለኃዘን ይሰጣል እንጂ በምንም ዓይነት ተመልሶ አይገኝም ።

ጊዜ ታላቅ ጸጋና የተፈጥሮ ስጦታ ነው ስጦታነቱም ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠ ነው ። በሚገባ የማይሠራበትና የማይጠቀምበት ሰው ቢኖር የእግዚአብሔርን ስጦታ በከንቱ አባክኖአልና ሳይቀጣ አይቀርም ።

በእያንዳንዱ ሰው ዘንድ የቲለያየ የሥራ ጊዜ አለ ለተማሪው የመማሪያና የጥናት ፣ ለገበሬው የመዝሪያና የመሰብሰቢያ ፣ ለነጋዴው የመግዣና የመሸጫ ጊዜ አለው ። ይሁን እንጂ የመማሪያው ጊዜ ከጥናቱ ፣ የመዝሪያው ወቅት ከመሰብሰቢያው የመግዣው ገበያ ከመሸጫው ልዩ ነው ። ሁሉም በየወቅቱ ጊዜውን ከሥራው ሥራውንም ከጊዜው ጋር በማገናኘት የሠሩ እንደሆነ አጥጋቢ ውጤት ያገኛሉ ። ብልህና አስተዋይ ሰው ጊዜን ከሥራ ሥራንም ከጊዜ ጋር ያገናዝባል ። የጊዜን ዋጋ ይገነዘባል ከትናንቱ ለዛሬው ከዛሬው ለነገ ይይዛል ጊዜንም ያለ ሥራ አይገድልም ።

አዲስ ሥራ ሠርተን አዲስ ሕይወት የምናገኝበት አዲስ ዓመት ነው መልካሙን ሥራ ሁሉ ለነገ(ለከርሞ) በማለት ቀጠሮ ልንሰጠውና ልናዘገየው አይገባንም የዛሬውን ዛሬ የነገውን ነገ ለመሥራት እንዘጋጅ ። ዛሬና ነገ በምንም አይገናኙም ነገ የእኛ ሳይሆን የሌሎች ይሆን ይሆናል ። ዛሬ ግን የእኛ ነው ይዘነዋል ፣ ነገር ግን ይዘን ልናቆየው አንችልምና በከንቱ ይዞን እንዳይጠፋ ሠርተን እንጠቀምበት ። ''ጊዜ ወርቅ ነው'' ተብሏል የወርቅ ፍልቃቂ ትንሽ እንኳ ብትሆን ከፍተኛ ዋጋ እንዳላት ሁሉ በሰኮንድና በደቂቃ የሚቆጠር ጊዜም ዋጋ ያለውና ከፍተኛ ሥራ ሊከናወንበት የሚችል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

በአዲስ ዓመት አዲስ ሥራ ሠርቶ አዲስ ሕይወትን ለመቀዳጀትና አዲስ ኅብረተሰብእን ለመመሥረት ትጋትንና ንቃትን ፣ ጥበብንና ትዕግሥትን ፣ መሻሻልንና ያለ መሰልቸት አዘውትሮ መሥራትን ገንዘብ ማድረግ ነው ። እነዚህ ጊዜ እንዳይባክን የሚረዱ የጊዜ መሣሪያዎች ናቸው ።

አሁን የምንቀበለው አዲስ ዓመት አዲስ እንደሆነ ቁሞ አይጠብቀንም ከርሞም ለማን እንደሚሆን አናውቅም ልናደርገው የሚገባንን ሁሉ ዛሬውኑ ልንፈጽመው ይገባል ። የዛሬው ትውልድ ሊፈጽመው የሚገባውን ለነገው ትውልድ የሥራ ውዝፍ ማቆየት ያስወቅሳል በጊዜው ሊሆን የሚገባውን በጊዜው ፈጽሞ መገኘት ግን ያስመሰግናል ። ተተኪውን ትውልድ ያኮራል ። ለሁሉም መሣሪያው ጊዜ ስለሆነ ጊዜ በከንቱ እንዳይባክን መጠንቀቅ ይጠቅማል ።



# የኒቅያ ጉባኤና ውጤቱ

ኒቅያ አሁን በቱርክ ግዛት ውስጥ የምትገኝ ስትሆን በአንድ ጊዜ እጅግ በጣም በርከት ያሉ ሰዎችን ለማስተናገድ የምትችል ሰፊና አማካይ ቦታ ናት።

ታላቁ ቆስጠንጢኖስ የሮማን መናገሻ ዋና ከተማ ወደ ቁስጥንጥንያ ካዛወረው ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የሃይማኖት ስብሰባ የተደረገው በኒቅያ ነው ።

ጉባኤው የተደረገው ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በ325 ዓ.ም. ሲሆን ለጉባኤው ምክንያት የሆነው የአርዮስ የጥርጥር ትምህርት ነበር አርዮስ እጅግ በጣም የተማረ ከመሆኑም ሌላ በእስክንድርያ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አለቃ ነበር ። ይኸው ምሁር ወልድ በመለኮቱ ፍጡር ነው የሚለውን ቃል ማንም ሳያስተምረው ከራሱ አንቅቶ ማስተማር ጀመረ ይህንን የኑፋቄ ትምህርቱን በይፋ ሳይሆን ውስጥ ለውስጥ በማስተማር በርከት ያሉ ተከታዮችን በማግኘቱ በግልጽም ባይሆን ውስጥ ለውስጥ በክርስቲያኖች ላይ መከፋፈልና መለያየት ደርሶባቸው ነበር ።

በዚያን ዘመን ለክርስቲያኖች ነፃነትን ያወጀላቸው ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ከነገሠ ሃያ ዓመታት ሆኖት ነበር ምንም ለክርስቲያኖች በነፃ አምልኮታቸውን እንዲፈጽሙ ቢፈቅድላቸውም የአርዮስ የክህደት ትምህርት አማኞችን የሚለያይና የሚከፋፍል በመሆኑ ኅዘን ሳይሰማው እንዳልቀረ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ይናገራል ።

ከብዙ ትዕግሥት በኋላ ቆስጠንጢኖስ የክርስቲያኖች እምነት በአንድ አቅጣጫ ብቻ መመራት እንዲችልና ሊቃውንቱም በትምህርት እንዳይለያዩ በአንድ ላይ ተሰብስበው ትክክለኛ የሆነ የሃይማኖት መመሪያ እንዲያወጡ አዋጅ አስነገረ ባስተላለፈውም አዋጅ መሠረት ከሚያዝያ ሃያ አንድ ቀን ጀምሮ እስከ መስከረም ሃያ አንድ ቀን ድረስ ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ዓርባ ሊቃውንት ተሰብስበው በሱባኤ እስከ ኅዳር ዘጠኝ ቀን ከቆዩ በኋላ አርዮስን ተከራክረው ፣ አውግዘውታል በቁጥር በርከት ብለው ከተሰበሰቡትም ሊቃውንት መካከል 318ቱ ሊቃውንት ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ ወልድ በመለኮቱ ከአብ ጋር ትክክል ነው በማለት እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ኅንደ አንድ ልብ መካሪ ሆነው ለጉባኤው ገለጹ ታላቁ ቆስጠንጢኖስም የእነርሱን ሃይማኖት በይፋ ተቀብሎ በአዋጅ ሁሉም ሰው እንዲቀበለው አደረገ ።

እነርሱም ከዚያ በኋላ ሃያ አንቀጾችን አውጥተው ለክርስቲያኖች መመሪያ እንዲሆኑ አድርገዋል ለክርስቲያኖች መመሪያ እንዲሆኑ ካወጧቸውም የሃይማኖት አንቀጾች አንዱ ጸሎተ ሃይማኖት ነው ። 318ቱ ሊቃውንት በአንድ አምላክ እናምናለን ከሚለው ጀምረው ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም እስከሚለው ድረስ ከመናገራቸውም ሌላ አርዮስንም ከጉባኤያቸው እንዲለይና የኑፋቄውንም ትምህርት እንዳያስተምር አውግዘው ለይተውታል ።

ይህም የሃይማኖት ጸሎት በእኛ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በዓለም አብያተ ክርስቲያናትም ዘንድ የኒቅያው ጸሎት በመባል የታወቀ ነው ቤተ ክርስቲያናችን የሊቃውንት ቅዳሴ በሚቀደስበት ጊዜ ይህ የሃይማኖት ጸሎት እንዲደገም ወስናለች ።

ቤተ ክርስቲያን ስብሰባዋን በኒቅያው ጉባኤ ብቻ አላበቃችም በየጊዜው እየተነሡ የኑፋቄንና የክህደትን ትምህርት የሚያሰራጩትን መናፍቃን ሁሉ ጉባኤ እያደረገች ለመመለስ የሚፈልጉትን በተግሣጽ ስታልፋቸው የማይመለሱትን ደግሞ በውግዘት ስትለያቸው ኑራለች ለምሳሌ መንፈስ ቅዱስ ሕሁፅ ብሎ የተነሣውን መቅዶንዮስን በ381 ዓ.ም. አሁን የቱሪክ ግዛት በሆነችው ቁስጥንጥንያ አውግዛ ስትለይ ፣ እንዲሁም ማርያም ወላዲተ ሰብእ ናት እንጂ ወላዲተ አምላክ አይደለችም በማለት ተነሥቶ የነበረውን ንስጥሮስን በ431 ዓ.ም. አውግዛ ለይታለች ለማስረጃ ያህል በዓለም አቀፍ የሚታወቁትን ጉባኤያት ጠቀስኩኝ እንጂ በተለያዩ ጊዜያት በርከት ያሉ ጉባኤያት መደረጋቸው የሚያጠራጥር አይደለም አሁንም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን የምትመራው በጉባኤ ስለሆነ በየጊዜው የሚገጥማትን ችግር ሁሉ የምታስወግደውና የሃይማኖትንም መመሪያ የምታወጣው በቅዱስ ሲኖዶስ መሆኑ የተረጋገጠ ነው ።

ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ረጋገጥን በዚያው በአድራሻዎ በፖስታ ቤት በኩል ቢከታተሉ ሊያገኙአቸው ይችላሉ ።

2ኛ በሐሙስ ዕለት የሚለው ቃል በቀሌምንጦስ ብቻ የተጻፈ አይደለምቀሌምንጦስ የጻፈው በኦ.ዘፍ.3.15 እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትነክሳለህ''የሚለውን ቃል መሠረት በማድረግ ስለሆነ ከትንቢቱ ተግባሩ ቀደመ ሊባል አይችልም ።

3ኛ ሰው በሰሌን መቀበር የጀመረው የሰው ልጅ በልብስ መጠቀም ከጀመረበት ዘመን ጀምሮ ነው የተጀመረበት ሀገርግን ተለይቶአይታወቅም አንዳንድ ሰዎች በሕንድ ሀገር ነው ሲሉ ሌሎች በቻይና ነው ይላሉ እንዲሁም በዓረብ ሀገር ነው የሚሉም አሉ ።

ይህ ሁሉ አስተሳሰብ ስለሆነ ከአንባቢያንም ስለዚሁ ሌላ መረጃ ያላችው ቢኖሩ በደስታ ተቀብለን ለማተም ዝግጁዎች ነን ።



www.ethiopianorthodox.org

## ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን



በወጣትነትህ ዘመን ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

አዘጋጅ ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

## ወጣቶች ከቡሄ እስከ መስቀል በዓል

በሀገራችን በሚከበሩት መንፈሳውያን በዓላት ሁሉ ወጣቶች ከዓዋቂዎች የተለየ ባህልና ሥርዓት እንዳላቸው የታወቀ ነው ፡፡ በዚህም መሠረት በዓመት ውስጥ ለምናከብራቸው መንፈሳውያን በዓላት ሁሉ ልዩ ልዩ ዝግጅት አድርገው ይቆዩና ወቅቱን በመመልከት ጨዋታቸውም ሆነ ዝግጅታቸው የተለያየ ቅርጽና ይዘት ይኖረዋል ፡፡

ከቡሄ እስከ መስቀል ባሉት በዓላት ማለት ለደብረ ታቦር ፣ ለቅዱስ ዮሐንስና ለመስቀል የሚጫወቷቸው ጨዋታዎች ለልደት ፣ ለጥምቀትና ለትንሣኤ በዓላት ከሚጫዋቷቸው ጨዋታዎች ጋር አይመሳሰሉም ፡፡ ስለሆነም ወጣቶች ከቡሄ እስከ መስቀል በዓል ድረስ የሚያደርጉት ዝግጅትና የጭወታ ዓይነት እንደየሀገሩ ባህል የተለያየ ቢሆንም ጥቂቱንና በአንዳንድ ሀገሮች ሲካሄዱ ያየናቸውን ለማስታወስ እንሞክራለን ፡፡

### የቡሄ ጅራፍ

የጅራፍ ማጮህ ጨዋታ የሚከናወነው ከቡሄ እስከመስቀል በዓል ባሉት ጊዜያት ሲሆን ይህ በዓል ከመድረሱ በፊት ወጣቶች ለጅራፍ የሚሆናቸውን ልጥ ለማግኘት ልጥ ያላቸውን እንጨቶች እየፈለጉ ይልጡና ያከማቻሉ ፡፡ በቆላማውና በወይና ደጋው ክፍል ያሉት ልጡን የሚያገኙት ከጠድቻ ከላንቁሶና ከውልክፍ ከሌሎችም እንጨቶች ሲሆን በደጋው ክፍል የሚኖሩት ደግሞ ከጓሳ ፣ ከቱቻ ሣርና ከፈረስ ጭራ ነው ፣ በዚህ ዝግጅት ከቆዩ በኋላ የቡሄ ዋዜማ ጅራፍ ይጉነጉናል ይገመዳል፤ እንዲጮህም ሆኖ ይዘጋጃል በከፍተኛ ድምጽም እንዲጮህ የሚያደርገውም በጅራፉ ጫፍ ላይ የሚገመደው ቃጫ ወይ የፈረስ ጭራ ነው ፡፡

የቡሄ በዓል ዕለት ከዘመድ አዝማድ፣ ከአበልጅና ከጎረቤት የሚመጣላቸውን የቡሄ ኅብስት እየያዙ አመቺ በሚሆን ሜዳ ላይ የአንድ አካባቢ ልጆች አንድ ላይ እየተሰበሰቡ ዳቧቸውን እያዋጡ /እየቀላቀሉ/ “ ቡሄ በሉ ልጆች ሁሉ” እያሉ ዳቧቸውን እየበሉ ጅራፋቸውን እያጮሁ ሲደሰቱ ይውላሉ ፡፡

በቀድሞ ጊዜ በአንዳንድ ሀገሮች በጅራፍ የመጋረፍ ባህል ስለነበር ወጣቶቹ ወገን ለይተው ቡድን አበጅተው ርስ በርሳቸው በጅራፍ ይጋረፉ እንደነበር ከአባቶች የሚነገር እውነተኛ ታሪክ አለ ፡፡ ይህም የሚሆነው በ1ኛ ደረጃ የወጣቶቹን ወኔ ለመፈተንና በጦርነትም ጊዜ ድፍረት እንዲኖራቸው ለማለማመድ ይመስላል ፡፡ በሌላ በኩል ግን ደም ካልፈሰሰ እህል ሊሆን አይችልም በሽታዎች ይበዙና ሰዎች ያልቃሉ ፣ጦርነት ይነሣና በሀገር ላይ ሰላም ይታጣል ወዘተ የሚሉትን ምክንያቶች በሚያስከትል አጉል ባሕልና ልማድ ነበር ይባላል ፡፡ ከዚህ የተነሣ ወጣቶች በጅራፍ የሚጀምሩት ግብግብ ወደ ኅልማሶቹ እየተዛመተ ጉራዴ እስከመማዘዝና ጥይት እስከመታኮስ እየደረሱ የብዙዎች አካል ከመጉደሉም በላይ በዚሁ መንሥኤ የሚሞቱ ብዙ ሰዎች እንደነበሩ ይነገራል ፡፡ ይህም በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በአዋጅ ተከልክሎ እንደቀረ አባቶች ይናገራሉ ፡፡ ይሁን እንጂ ጅራፍ የማጮሁ ባህል አሁንም በአብዛኛው በባላገር ያሉ ወጣቶች ዘንድ የማይቋረጥ ነው ፡፡ ስለሆነም ጅራፍ የሚያገለግለው ከቡሄ እስከመስቀል በዓል ስለሆነ ለቡሄ ለቅዱስ ዮሐንስና ለመስቀል እያጮሁ ከተጠቀሙበት በኋላ ለእርሻ በሮች መግረፊያና ለከብት ማሠሪያ ይሆን ዘንድ ወጣቶቹ ለቤተሰቦቻቸው ይሰጧቸዋል ፡፡

### የችቦ መብራት

የችቦ አበራር ባህልም ለቡሄ ፣ ለዘመን መለወጫና ለመስቀል በዓል የሚፈጸምና የተለመደም በመሆኑ በከተማም ሆነ በገጠር ያሉ ወጣቶች ለመብራት የሚሆን ችቦ በማዘጋጀት በኩል ታላቅ ድርሻ አላቸው ፡፡ በተለይም በባላገር ያሉ ወጣቶች ችቦውን የሚያዘጋጁት እንደከተማዎቹ ወጣቶች በቀላሉ ከባህርዛፍ ቅጠልና ጭራሮ ሳይሆን ከእንጨቶች መካከል ለዚህ ተግባር አመቺየሆኑትን እየቀጠቀጡ የሚያዘጋጁት ገና በበጋው ወራት ነው፡፡የመብራቱ ምሥጢርና ምሳሌውም ደግሞ ብሩህ ወደሆነው አዲስ ዘመን በሰላም አሸጋግረን እያሉ መጭውን ዓመት ብሩህ በሆነ ተስፋ ለመቀበል ነው ፡፡ የደመራ ዕለትም የብርሃነ መስቀሉንና የደመራውን ታሪክ በማስታወስ በየደጁ ሲበራ ለዚህ ተግባር ግንባር ቀደም የሚሆኑት ወጣቶች ናቸው ፡፡

### የሆያ ሆዬ ጨዋታ

ከቡሄ እስከ መስቀል ባሉት ዕለታት በባላገር ያሉ ወጣቶች ቀንና ሰዓት እየቀጠሩ በበዓላት ቀን ማታ ማታ እየተሰበሰቡ በየመንደሩ በመሄድ የሆያሆዬ ጨዋታ ይጨፍራሉ ፡፡ በዚህ ጨዋታ ልምምድና ችሎታ ያላቸውና ምራቃቸውን የዋጡ ጠንከር ያሉ ወጣቶች ተመርጠው ጨዋታውን እንዲመሩ ይደረግና በነሱ ግንባር ቀደምትነት ተራ በተራ በየመንደሩ እየዞሩ ይጨፍራሉ በጨዋታው ወቅት አለመግባባት ቢፈጠር የሚዳኙ ገንዘብ የሚቀበሉና የሚይዙ እነዚያው ናቸው ፡በአንዳንድ ሀገር ጨዋታው የሚጀመረው በቡሄ ዕለት የሚፈጸመው ለመስቀል ሲሆን በአንድ አንድ ሀገር ደግሞ ከቅዱስ ዮሐንስ እስከመስቀል ነው ፡፡

በጨዋታው ወቅት ማለት ወጣቶቹ በየመንደሩ እየዞሩ በሚጨፍሩበት ጊዜ በመንገድ ሳሉ ፣ ከሰው ቤት ሲገቡና ሲወጡ ፣ ገንዘብ ሲቀበሉ ወይም ሲያጡ የሚጨ ወቷቸው ጨዋታዎችና የሚገጥሟቸው ግጥሞች የተለያዩ ስለሆኑ ከመንገድ ላይ መሆናቸውን ወይም ከሰው ቤት መግባታቸውን ማግኘትና ማጣታቸውን ጭምር በሩቅ ሆነው የሚያዳምጡ ሁሉ በቀላሉ ሊያውቁ ይችላሉ ከበሩ ሲገቡ ጀምረው እስከ ሚወጡበት ጊዜ ድረስ የባለቤቱን የሚስቲቱንና የልጆቹን ስም እየጠሩ ያሞግሳሉ አሞግሰውና ጨፍረው ሳይሰጥ ካስናበታቸው በግጥም እየተሳደቡ ይወጣሉ እንዲያውም በቀድሞ ዘመን ከቤት ከወጡ በኋላ ገንዘብ የከለከላቸውን ሰውዬ ስም እያነሱ ከማልቀሳቸውም በላይ ማዶ ለማዶ ሆነው በከፍተኛ ድምጽ “እገሌ ሞቷልና አላቅሱኝ ተብላችኋል” እያሉ እየተጠራሩና እያረገዱ ሙሾ እያወጡ እያለቀሱ በቤቱ አካባቢ መቃብር ቆፍረው በሰውየው ምሳሌ አንድ ነገር ቀብረው ይሄዱእንደነበርና ያምቦታ የእገሌ መቃብር እየተባለ ይሰየም እንደነበር ይነገራል ፡፡ ይህም በመሆኑ ሰዎች ሁሉ ስማቸው እንዳይጠፋና ሰው እንዳይስቅባቸው ወጣቶቹ በሚጨፍሩበት ጊዜ በአክብሮት ተቀብለው ያቅማቸውን ሰጥተው ይሸኛሉ እንጂ አይከለክሉም ነበር ፡፡ አሁንም ሰው የመሰደቡና በቁም የመቀበሩ ጉዳይ ይቅር እንጂ የሆያሆዬ ጭፍራ በአንዳንድ ሀገሮች እስካሁን ድረስ ያልቀረ መሆኑ የተረጋገጠ ነው ፡፡

ከመስቀል በዓል በኋላ ጭፋሮው ሲያከትምና መንደሮቹ ሲዳረሱ ያለው ገንዘብ ተቆጥሮ እንደ ገንዘቡ ብዛትና ማነስ እንደጨፋሪውም ሰው ብዛት ተተምኖ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሰንጋ ይገዛና በጭፋሮው የደከሙት ወጣቶች ብቻ ተሰብስበው በጫካ ውስጥ ወይም በባዶ ቤት አርደው ያንን ራሳቸው ተራ በተራ እየቀቀሉ እስካለቀ ድረስ እየዘፈኑ እንዲበሉ ይደረጋል ፡በመጨረሻም ሥጋውን ሲጨርሱ ቆዳው ለጠፍር ይሆናቸው ዘንድ ሰንጥቀው ያንን በእጣ ተከፋፍለው ይለያዩና ጠፍሩን አልፍተው ለቤተሰቦቻቸው ያበረክታሉ ራሳቸውን ችለው በትዳር ላይ ያሉትም ለምራን ፣ ለማነቆና ለመርገጥ ለጅራፍና ለመጫኛ እያደረጉ እራሳቸው ይጠቀሙበታል ፡፡

### ሴቶች ወጣቶች በዕንቁጣጣሽ

በየዓመቱ የዕንቁጣጣሽ እለት ልጃገረዶች ሁሉ በአንድነት ተሰብስበው “እንቁጣጣሽ እንኳን ደህና መጣሽ በአበባ አሸብርቅሽ” እያሉ በመዝፈን በዓሉን በደስታ ያሳልፉታል ፡ይልቁንም በአንድ ላይ ከተሰበሰቡ በኋላ“ አበባዬ ሆይ ለምለም” እያሉና ሌላም ዘፈን እየዘፈኑ በሠፈራቸው ውስጥ ባሉት መንደሮች እየገቡ ገንዘብ ይሰበስባሉ ልጃገረዶቹ በመንደር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ በከተማ ውስጥ ያሉ እናቶች ገንዘብ ሲሰጡ በገጠር ያሉት ግን እህል ፈትልና ጥጥ የመሳሰሉትንም ጭምር ይሰጧቸዋል እነሱም ይህንን ተቀብለው ከመከፋፈላቸው በፊት ካገኙት ነገር ሁሉ ከፍለው በሠፈር ውስጥ ጧሪ ለሌላቸው ባልቴቶች የሚሰጡ አሉ ፡፡

ይህ ሁሉ ከባህላችን ጥቂቱ ክፍል ስለሆነ መጥፎው ታርሞ የሚሻሻለው ተሻሽሎ ለአሁኑ ትውልድና ለአለንበት ዘመን ተስማሚ የሆነው ተበጥሮና ተንጠርጥሮ በሥነ ሥርዓት እንዲካሄድ ቢደረግ ለወጣቶቹ መዝናኛ ከመሆኑም በላይ የአባቶችንም ባህልና ታሪክ ለማስታወስ ሊጠቅም ይችላል ፡የጅራፍ ማጮሁና የሆያሆዬው ጭፈራ በከተማ ውስጥ አስቸጋሪ ይመስላል ምክንያቱ ቀደም ባለው ጊዜ እንዳየነው በየመንገዱ የሚጮህው ጅራፍ ጆሮ እያደነቆረ አላፊ አግዳሚውን ያስቸግር እንደነበር የሚታወስ ነውና እንዲቀር መደረጉ አግባብ ነው ፡፡ የሆያ ሆዬ ጭፈራውም እንዲሁ የሚያስከትለው ችግር አለ ፡፡ ይኸውም በከተማ ውስጥ ብዙዎች ርስበርሳቸው ለመተዋወቅ ስለማይችሉ ከየጉዳናው እየተጠራቀሙ ስለሚጨፍሩ ከነሱ ጋር ማን አብሮ እንዳለ ባለመታወቁ ለሌባ አመቺ መንገድ ከመፍጠሩም በላይ ጨፋሪዎችም ቢሆኑ በገንዘብ ክፍያው እየተጣሉ መደባደባቸው አልቀረም በዚህ ግርግር ጉልበት ያላቸው ብቻ ገንዘቡን እየተናጠቁት ስለሚሄዱ አቅመ ደካማው ወጣት ተርፉ ጩኸት ብቻ ነው ስለዚህ ባሕሉም ሆነ ሥርዓቱ እንደገጠሩ ስላልሆነ ከአባቶች ባህል ውጭ ነውና ቢታሰብበት መልካም ነው ፡፡





www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

## መምህር ትርፌ ንባቡ

በሊቅነታቸው በጣም የታወቁት መምህር ትርፌ ንባቡ የትውልድ አገራቸው በጐጃም ክፍለ ሀገር ከአቡነ ሲኖዳ ገዳም ደብረ ዕሙና ነው ።

የመጀመሪያውን የትምህርት ደረጃ በተወለዱበት አካባቢ ከአጠኑ በኋላ በዚያው ክፍለ ሀገር ወደሚገኙት አውራጃዎችና ወረዳዎች እንዲሁም በየገዳማቱና በየአድባራቱ እየተዘዋወሩ ቅኔ ከነአገባቡ አጥንተው ለመምህርነት ተመርቀዋል የሐዲሳትንና የብሉያትንም ትርጓሜ ተምረው አውቀዋል ።

በዚህ ዓለም በሕይወተ ሥጋ የኖሩበት ዘመን ከዚህ እስከዚህ ተብሎ ተለይቶ ሊታወቅ ባይቻልም ከዘመነ መሳፍንት እስከ ዓፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት አጋማሽ መኖራቸው በታሪክ ተከታታዮች ተረጋግጧል ።

የዓፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ከ1863 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1881 ዓ.ም. ሆኖ የነገሡትም አሥራ ስምንት ዓመት እንደነበረ የታሪክ ዘገባዎች ስለሚያረጋግጡ እንግዲህ የመምህር የዕድሜ ገደብ በ1872 ዓ.ም. ላይ ተፈጽሟል ማለት ነው ።

መምህርትርፌ በትውልድ አገራቸው በደብረ ዕሙና ቅኔ ከነአገባቡ ኀንዲሁም የአርባ ስድስቱን መጽሐፍተ ብሉያት ትርጓሜ በማስተማር ለብዙዎች ደቀ መዛሙርቶቻቸው ሊቅ የሚያሰኘውን የከፍተኛ ትምህርት ስም አተዳጅተዋቸዋል ።

ለመምህር ትርፌ መመስገንን መወደድንና መከበርን አትርፈውላቸው ከነበሩት ምክንያቶች ዋነኛው አእምሮዋቸውን በየአስተማሪዎቻቸው የትምህርት ይዘት ብቻ አሥረውና ባለህ እርጋ ብለው ከግል ምርምርና አስተያየት አለመታገዳቸው ነው ከዚህም የተነሣ በጐጃም በሸዋ በጐንደር ከሚገኙ ሊቃውንት አብዛኛዎቹ በአሥራወ መጻሕፍት ይዘታቸውና በምሥጢረ መጻሕፍት ምርምር ስልታቸው እየተሳቡ ጉባኤያቸውን ለጥያቄ ይከቡት እንደነበርና በሚሰጣቸውም በቂ የሆነ መልስ እየተደሰቱ እንደሚመለሱ ይነገራል ።

መምህር ትርፌ መምህርነታቸው ለደብረ ዕሙና ገዳም ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ የሚኖሩት በዲማ ነበር ።

በጊዜ ሞታቸው ስለቀብራቸው የሰጡት የኑዛዜ ቃል

መምህር ፣ በመማር ፣ በማስተማርና በገዳማዊ አስተዳደር ሕይወታቸውን ሲመሩ ከኖሩ በኋላ በእርጅናቸው ምክንያት ሞት የቀረባቸው መሆኑን ተገንዝበው በጊዜ ሞታቸው ሥርዓተ ፍትሐት በዲማ እንዲደርስላቸው በደብረ ዕሙና ገዳም ሥርዓተ ቀብር እንዲፈጸምላቸው የኑዛዜ ቃላቸውን ለዘመዶቻቸው ለደቀ መዛሙርቶቻቸውና ለወዳጆቻቸው አስተላለፉ ።

ለዚህ ኑዛዜአቸው መነሻ የሆናቸውን ምክንያት አስመልክተው ታሪክ ተከታዮች ሲያስረዱም መቃብሩ ደብረ ዕሙና እንዲሆን ማለታቸው አገሩ በጠፍነቱ የታወቀ እንደነበረ ቢነገርም ለሰው መቃብሩ በአገሩ ቢሆን መልካም ነው ሠናይ ለብእሲ ለእመኮነ መቃብርቱ ውስተ ርስቱ የተባለውን መሠረት ለማድረግና ፈር ለማስያዝ፡ሥርዓተ ፍትሐት በዲማ ይፈጸምልኝ ማለታቸውም ዲማ ብዙዎች ሊቃውንት ካህናት ደቀ መዛሙርት ያሉበት ከመሆኑም ጋር በልዩ ግምጃና ሐር የተጌጠ ድንኳን ተተክሎ አስከሬናቸው ያረፈበት አጎበር በወርቅ መጐናጸፊያ ተከልሎ አብዳላክኒና ሐር ቀሚስ የለበሱ መነኮሳት ቀሳውስት ዲያቆናት የብርና የወርቅ መስቀል ይዘው በማዕጠንት እንዲያጅቧቸው ሊቃውንቱ መዘምራኑ ለሞያቸው ለታሪካቸው ተገቢ የሆነ ዝማሬ እየዘመሩ ይበል የሚሰኝ ተስማሚ ቅኔ እየተቀኙ የብር ከበሮ እየመቱና እያጓደዱ እንዲፈቷቸው ነው ይላሉ ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ መምህር በሕይወተ ሥጋ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ ለሰው ታላላቅ ቀናት አሉት እነዚህም አንደኛው የሚወለድበት ሁለተኛው ሥርዓተ ጋብቻ የሚፈጸምበት፣ሦስተኛው ከሕይወተ ሥጋው በሞት ተለይቶ ወደመቃብር ዓለም የሚወርድበት ናቸው ማለትን አዘውትረው በጉባኤያቸው ሁል ጊዜ ይናገሩ እንደነበረ ይተረካል ።

ይሁን እንጂ መምህር ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩበት ጊዜ የዲማ ሊቃውንትና ካህናት በደብረ ዕሙና እንድቀበር ሲሉ ገና በሕይወት ሳሉ መናዘዛቸውን አልተገነዘቡም ነበርና ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ሁሉ ለከፍተኛ ለሊቅነታቸው ተገቢ የሆነ መዝሙር እየዘመሩ ቅኔ እየተቀኙ ካህናተ ሰማይን በመሰሉና እጅግ የሚያስደንቅ ልብሰ ተክህኖ በለበሱ ካህናት እያሳጀቡ ሲፈቱ ከዋሉ በኋላ አስከሬናቸውን ወደተዘጋጀለት የቀብር ቦታ ሲያጉዙ የመምህራችንን ሬሣ ከዚህ አናስቀብርም በማለት የደብረ ዕሙና ሕዝብ በሙሉ ጦር ሠርቶ እጅግ በሚያስገርም ሰልፍና ፉከራ ከዲማ ደረሰ።ሰልፉም ከዚያው ከመካነ መቃብሩ አቅራቢያ እንደተጠጋ መምህራችን ከደብረ ዕሙና እንጂ ከዚህ አይቀበሩም ይቀበራሉ በማለት በዲማ ሕዝብ በኩል በፍጹም ያልተጠበቀ ጠብ ተቀሰቀሰ።በዚህምጊዜየዲማሕዝብ የእኛ ታቦት ጣዖት ነውን ? ከዚህ የማይቀበሩበት ምክንያት ምንድነው? ብሎ ሰልፉን በሰልፍ ለመመከት ወዲያውኑ ተዘጋጀ ከሁለቱም በኩል አሥራምስት ሰው ያህል ስለሞተ በየበኩላቸው ሬሣቸውን እያነሡ መላቀስ ሆነ ።

በዚህም ጊዜ የጫወታ ለዛ የነበራቸው ራቅ ማስሬጐብዜ እንዲህ ሬሣ በየደጁ ሊተርፍ በአንድ ሬሣ እርስበርሳችን ተጣላን ? ብለው ተናገሩ እየተባለ ይተረካል ።

መምህር ትርፌ የሚያመሰግናቸው የትምህርት ጉባኤያቸው ስፋትና የመን

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

«እንግዲህ ያየኸውንና አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ የሚሆነውን ነገር ሁሉ ጻፍ » ራእ . 1 ፥ 19

የድርሰት መሠረታዊ ትርጉም

«ድርሰት »ዓይን ያየውን፣ ጆሮ የሰማውን ወይም በአምስቱም ሕዋሳተ አእምሮ መርምረው የተረዱት የአንድ ዓይነት ድርጊት አፈጻጸም በአእምሮ ጽንስ በብርዕአማካይነት የሚወለድ የምርጥ ቃላት ሥዕል ነው።

በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ከተሰጠው የትርጉም ትንታኔ በከፊል«ድርሰት ማለት ምሥጢሩ የሚያጠግብ፡ኀይለቃሉ የሚያረካ፡ጣዕመ ቃሉ ልብን የሚነካ ፡ አእምሮን በደስታ የሚያፈካ ፣ ቀስቃሽ ስብከት ፡ ትርጓሜ ፡ ድስኩር ፣ መዝሙር ፣ ጉሥዐተ ልብ ከልብ ወይም ከአእምሮ የሚመነጭ የእምሮ ጭማቂ ነው የሚል ዓይነት ሐሳብ ይገኝበታል ።

«ድርሰት »የሥነ ጥበባት ሁሉ ምንጭ የአእምሮ ብርሃን ፣ የኅሊና መሪ ፡ ባጠቃላይ አገላለጥ የሰውን መንፈስ በዕውቀት እየመገበ ሕይወትን በማደስ አእምሮን የሚያኅለምስ የተከበረ መና ነው » ከበደ ሚካኤል ሥ.ማ.ም.

በመሠረቱ ፡ -የክርስቲያናዊ ድርሰት ወይም ድርሳን ዋና ዓላማ ና ተግባሩ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፉት የቅዱሳት መጻሕፍት ታሪካዊ ምሥጢራት ግልጥነት ባላቸው ምርጥ በሆኑ ውብ ቃላት እየተተረረጎሙ በልዩ ልዩ የሥነ ጽሑፍ መገናኛ ዘዴዎች ማለትም በመጽሐፍ መልክ በመጽሔትና ጋዜጣ ፣ በሬድዮ በሥዕላዊ መግለጫና የመሳሰሉትም ሁሉ የአማኞችን አእምሮ መመገብና ማኅለመስ የሚያስችል መንፈሳዊ ጥበብን ማስተማር ነው ።

አስረጅ ፡ - «እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ አንባቢው እንዲፈጥን በሰሌዳ በጽላት ላይ የምትጽፈውን የራእዩ ቃል ግልጥ እንዲሆን አድርገው » ይላል። ትንቢተ ዕንባቆም 2 ፥ 2 ።

ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ 14 ፥ 26 «ወንድሞች ሆይ ! በምትሰበሰቡበት ጊዜ ከናንተ አንዱ የመዘመር ፣ ሌላው የማስተማር ስጦታ ሲኖረው አንዱ ደግሞ ሥውር የሆነውን ነገር የመግለጥ ስጦታ ይኖረዋል፣ አንዱ ባልተለመደ አዲስ ቋንቋ የመናገር ስጦታ ክርስቲያኖችን የሚያንፅ መሆን አለበት » የሚል ቃል ይገኝበታል ። በግዕዙ በተለይ «ወዘምድራሳት » የሚል ቃል የሚገኝ ሲሆን ትርጉሙ«እንደ ሊጦንና መስተብቍዕ ወይም ኪዳንና ዘይነግሥ የመሳሰሉትን ድርሳናት የሚያመለክት ነው »

ሲሉ መተርጉማን ገልጠውታል።

ሌላው ጉልህ ማስረጃ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ስመ ጥሩ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅ ያሬድ ከሺህ ዓመታት በፊት የቀመረው የጻፈው መጽሐፈ ድጓ ነው ፡ ከመላው ዓለም መንፈሳውያን ድርሳናት መካከል ተወዳዳሪ አይገኝለትም ለማለት የሚያስደፍር ይህ ግዙፍ የሆነ የዜማ መጽሐፍ በመጻሕፍተ ብሉያትና ሐዲሳት መካከል ያለውን የምሥጢር ግንኙነትና ግንዛቤ በትርጉም እያጎላ በመግለጥ ጣዕም ባለው ዜማ ከነምልክቶቹ ከናታ ጋር አቀናብሮ ይዞ የተገኘ የመጻሕፍት ሁሉ መጽሐፍ ነው ። ስለዚህም ቅ ያሬድ የፀዋትወ ዜማ ድርሰት የቅኔና የትርጉም አባት ተብሎ ሊጠራ ይገባዋል ።

ከዚህም ጋር የሐዋርያትን ቅ ሲኖዶስ ሃይማኖተ አበው መጽሐፈ መነኮሳት ፍትሐ ነገሥት ፡-መጽሐፈ ምሥጢር መጽሐፈ በረዓለም ወዘተ የመሳሰሉትን ግዙፋን ድርሳናት ብንመረመር መሠረታቸው ቅዱስ መጽሐፍ ሆኖ የብሉያትን እና የሐዲሳትን ትርጉም ማንፀባረቂያ መሆናቸውን በቀላሉ እንገነዘባለን ።

ይህም ሁሉ የሚያስተምረን ክርስቲያናዊ ድርሰት የመጻሕፍተ ብሉያትና ሐዲሳት ምሥጢር መከሥት ወይም ገላጭ መሆኑን ነው እንግዲያውስ ጥሩ ልምድ ያለው ክርስቲያን ደራሲ ማለት የቅዱሳት መጻሕፍትን ብሉያትን ሐዲሳትን ሌሎችንም የሊቃውንት መጻሕፍት ምሥጢር ጊዜው በሚፈቅደው ዘመናዊ የአቀራረብ ዘዴ ብሩህና ውብ በሆኑ ምርጥ ቃላት በቀላል ቋንቋ እየተረጎመ ና እያብራራ መንፈሳዊ ትምህርትን የሚመግብ መምህር ማለት መሆኑን በቅድሚያ ልንጠቁም እንወዳለን ።

ስለዚህም ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት እየታተመ በሚወጣው በዚሁ መጽሔት አማካይነት በተከታታይ የምናቀርበው የዚህ ዓምድ ዝግጅት ክርስቲያናዊ የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ ወይም የስብከት ዘዴ የመሳሰሉትን መመሪያዎች የሚይዝ ስለሆነ አንባቢዎች የሚኖራችሁን አስተያየትና ጥያቄም ጭምር ሲኖራችሁ እንድትልኩልን በተስፋ እንጠባበቃለን ።

ቄ ፣ መክብብ አጥናው



www.ethiopianorthodox.org

# በሲዳሞ ክፍለ ሀገር የጌዲኦ ብሔረሰብእ ባሕል

በደቡባዊ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ክፍላተ ሀገር መሃል ሲዳሞ አንደኛው ነው ። የሲዳሞ ክፍለሀገር ስድስት አውራጃዎች አሉት ከእነዚህም አንዱ ጌዲኦ የሚባለው ነው ብሔረሰብኡም በዚሁ ስም ይታወቃል በዚህ ክፍለ ሀገር በሚገኙ አውራጃዎች ውስጥ ተሰባጥረው የሚኖሩ ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ያሉ ሲሆን እነዚህም የጌዲኦ ፣ የሲዳማ የአማሮ ኮይራ የጎጂና ቦረና የቡርጂ ፣ የመርሐን የሎሳን ፣ ገረመሮና ዲጎዳይ የተባሉ ይገኙበታል። ገሚሶቹ ብሔረሰቦች በደጋውና በወይና ደጋ የሚኖሩ ሲሆኑ ፣ የተቀሩት በቆላው አካባቢ ኑዋሪ ናቸው ። ደጋና ወይና ደገኞቹ በእርሻና በከብት ርቢ የተሰማሩ ሁነው ሳለ ፣ ቆለኞቹ ደግሞ ብዙ የቀንድ ከብት በማርባት እንዲሁም ግመል ይዘው በመዘዋወር በዘላንነት ቆይተዋል ።

የሲዳሞ ክፍለ ሀገር በልምላሜ ያጌጠ ከመሆኑም በላይ ልዩ ልዩ የምርት ዓይነቶችን ሰጪ በሆነው ለም አፈር የታወቀነው በተለይም ደህና የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝልን የቡና ሰብል ከሚመረትባቸው ክፍላተ ሀገር ሲዳሞ ዝነኛው ነው ። በዚሁ መጠን የእህል ዘር በያይነቱ እንዲሁም ፍራፍሬዎች ይመረታሉ ። በሲዳሞ ክፍለ ሀገር በቡናና በእህል ዘር ምርቶች ከታወቁት አውራጃዎች አንዱ ጌዴኦ ነው ።

## የጌዲኦ ብሔረሰብ የቀድሞ ሥርዐትና አስተዳደር

በቀድሞ ዘመን የጌዲኦ ብሔረሰብ ሥርዐትና አስተዳደር ይመራ የነበረው ከየጎሳው በጥቆማ በሚመረጡ ሽማግሌዎች ነበር ። እነዚህም ሽማግሌዎች የቦሔረሰቡን የሞራል የሥራ ፣ የቤተሰብ የበዓላት የዳኝነትና የመከላከያ ሥርዓት በማውጣት ያስተዳድሩት ነበር ። እነዚህም የሕዝብ ተመራጭ የሆኑ መሪ ሽማግሌዎች የተመረጡለትን ተግባር ከመጀመራቸው በፊት በመረጣቸው ሕዝብ ፊት ቀርበው ያለአድልዎ በቅንነት በእኩልነት በፍትሕ እንደሚመሩት ቃላቸውን በመሃላ ያፀናሉ። ብሔረሰቡ እነዚህን ከመሃሉ መርጦ የሾማቸውን መሪዎች በየስድስት ዓመት እየሻረ በምትካቸው ሌሎችን ይሾማል ። እነዚህ መሪዎችም የሕዝቡን ጉዳይ ሸንጎ በመባል በሚጠራ ቤት ውስጥ ያዩለታል የሸንጎ ቤቱ የሚሠራው በአውራ ጎዳና ዳር ሆኖ አገልግሎቱም ለችሎት ብቻ ሳይሆን ለበዓላት ማክበሪያና ለመዝናኛ ለእንግዶችም ማረፊያ ነበር።

## በጌዲኦ ብሔረሰብ ዘንድ የቤተሰብ ሁኔታ

በብሔረሰቡ ባህል መሠረት ቤት ትዳር ያቋቋሙ ልጆች ሳይቀሩ የዕለት ከዕለት ኑሮአቸው ከወላጆቻቸው ጋር የተሣሰረ ነው ። ስለሆነም አባት ወንድ ልጆች ሲደርሱለት ከማሳው ቆርጦ በአካባቢው ቤት እንዲሰሩ ይሰጣቸዋል ቤት ይሠራሉ፤ የነርሱም ልጆች ለዚህ ሲደርሱ ሳይርቁ ትዳራቸውን በዚሁ ዓይነት ይመሠርታሉ።እንግዲህ እነዚህ ሰዎች የሚኖሩበት አካባቢ አንድ ትልቅ መንደር ይሆናል ማለት ነው ። ወላጆች በቢታቸው የሚያዘጋጁትን ልጆቻቸውን ጠርተው አብረው ይመገባሉ ልጆችም እንደዚሁ ቤታቸው ያፈራውን አምጥተው ከሽማግሌዎች ጋር ይበላሉ ይጠጣሉ። ይህ በየጊዜው የሚፈጸም የባህል ግዴታ ነው ። በዚህ ዓይነት ሽማግሌዎች የሆኑ ወላጆች በእድሜ ምክንያት በቤት ቢውሉም የልጆቻቸው እርዳታና ጨዋታ ምን ጊዜም ስለማይለያቸው በዚህ ይጽናናሉ ።

## ልጆች ሲወለዱ

የአረገዘች ሴት የመውለጃዋ ጊዜ ሲቃረብ ድጋፍ ሊሰጡዋት የሚችሉ የምግብ ዓይነቶች ይዘጋጁላታል ። ምግቦቹ፡ ገብስ ለገንፎ ፣ ሥጋ ፣ ቅቤ ማር ፣ ይሆናሉ ። ነፍሰ ጡርዋ እንደተገላገለች ባስቸኳይ ገንፎ ተገንፍቶ በቅቤ ይደረግና ማሩ ተበጥብጦ ብርዙ ይሰጣታል። የተወለደው ሕፃን ለጎረቤት የሚነገረው ግንድ ሲመታ በሚሰማ ድምፅ ስለሆነ ግንድ ተፈልጎ የተወለደው ህፃን ወንድ ከሆነ አራት ጊዜ ሴት ከሆነች ሦስት ጊዜ በመጥረቢያ ይመታል።ጎረቤቱም ትርጉሙን በዚሁ ተረድቶ ለጥየቃ ይመጣል ህፃኑ ከተወለደበት ወቅት ጀምሮ በየተራ የሚፈጸሙ ባህላዊ ሥርዐቶች ስላሉ ሥነሥርዐቶቹ እስካበቁ ድረስ የእመጫትዋ ባለቤት ለሰባት ቀን አብሯት ይቆያል ከዚያም ሺታ ማለትም አዲስ ሰው ተፈጠረ ለተባለለት ህፃን ቤተሰቡ በተሰበሰበበት በይፋ ቋሚ ስም ይወጣለታል ።

## የጌዲኦ ብሔረሰብ የጋብቻ ሁኔታ

በጌዲኦ ብሔረሰብ ዘንድ ወጣቶች የሚጋቡት ለአካለ መጠን በሚገባ መድረሳቸው ሲረጋገጥ ነው ። የሚፈጸሙትም የጋብቻ ዓይነቶች በሦስት ሊከፈሉ ይቻላል ።

1ኛ በልጁና በልጅቱ ወላጆች መሃል በሚደረግ ስምምነት የሚፈጸም ነው ።

2ኛ ሁለቱ ወጣቶች ተፈቃቅረው በስምምነት የሚፈጽሙት ጋብቻ ሲሆን ይህን የመሰለ የጋብቻ ሁኔታ በተደረገ ጊዜ የልጅ አባት ሽማግሌዎች ይዞ ወደ ልጅቱ አባት ዘንድ ሂዶ ጋብቻው እንዲጸድቅ ይደረጋል ።

3ኛ ሌላው የጋብቻ ዓይነት ልጅትዋ ሳትፈቅድና ወይም ወላጆችዋ ሳይጠየቁ ጎረምሳው የሚፈጽመው የጠለፋ ጋብቻ ነው ። እንዲህ ያለው ጋብቻ የተፈቀደ ባለመሆኑ እርቅ ከመደረጉ በፊት ወላጆች ሁኔታውን ከስሙ ግጭት ሊያስከትል የሚችል ነው ። ሆኖም የልጁ አባት ቶሎ ብሎ ሽማግሎች በመሰብሰብ ልጅቱ አባት ቤት ድረስ ሂዶ ከተማጠነና ካሣ ከከፈለ እርቅ ሊወርድ ይችላል ።

በተለይ በልጁና በልጅቱ ወላጆች መሃል በሚደረግ ጥያቄ የሚፈጸመው የጋብቻ ዓይነት ብዙ ውጣ ውረዶች አሉበት በመጀመሪያ የልጁ አባት ለአካለ መጠን የደረሰውን ልጁን ለመዳር በሥራ ወዳድነትና ባህልን በመጠበቅ ከታወቀ ቤተሰብ ለልጁ የምትሆነውን ልጅ ካገኘ በኋላ ከቤተዘመዱ ጋር ይወያይበታል ።ከዚያም ልጅቱን ለልጁ ለማጨት ሦስት ሽማግሌዎች አስከትሎ ወደ አባትዋ ቤት ይሄዳል በጉዞ ላይ ሳለም የተልእኮውን መሳካት ወይም አለመሳካት ይተረጉም ልኛል ብሎ የሚያምንበትን ፈር የተባለ ወፍ ድምጽ እያዳመጠ ይጓዛል ። በጉዞም አቅጣጫ በግራ በኩል ሆኖ ከጮኸ ልጅቱ ለልጁ ሚስትነት የማትበጅ መሆንዋ በወፍ ቋንቋ እንደተነገረው አድርጎ ይቀበለዋል ዳሩ ግን በሚሄድበት አቅጣጫ በቀኝ በኩል ወፉ ከጮኸ ጉዞው ፍሬያማ እንደሚሆን አድርጎ ያምናል ። የልጅቱ አባትም ይህን በመሰለው ድርጊት ስለሚያምን ወፍ ምን አለ ሲል እንግዶቹን ይጠይቃቸዋል ።

እንደዚሁም የልጁ አባትና የተከተሉትም ሽማግሌዎች ሲጓዙ ሚዳቋ ካቋረጠቻቸው ጉዞአቸውን ትተው ወደ ቤት ይመለሳሉ ምክንያቱም ሚዳቋ ደረቅ ስለሆነች ወጣቶች ሲጋቡ ሀብተ ቢስ ይሆናሉ አይወልዱም ብለው ያምናሉ ። ሙሉ እንስራ ውሃ የተሸከመች ሴት ካጋጠማቸው ደስታቸው ወደር የለውም ። « የተጋቢዎቹ ሕይወት በሀብት የተሞላ ይሆናል » ይላሉ ።

እነዚህን ምልክቶች ሁሉ አልፈው ከልጅቱ አባት ቤት ማለዳ ሲደርሱ የቤቱ በር ክፍት ሆኖ ከቆያቸው እሳቱ እየነደደ ከሆነ የምትታጨው ልጅ ቡና የምትቆላ ከሆነ፣ ወይም ውሃ ቀድታ ስትመጣ፣ በአጠቃላይ መላ ቤተሰቡ በእንቅስቃሴ ላይ ሳለ ከደረሱ ተልእኮአቸው በመልካም አጋጣሚ ላይ እንደተመሠረተ አድርገው ያምናሉ ። በዚህ ዓይነት ጉዞና አጋጣሚ ከልጅቱ አባት ቤት ሲደርሱ የልጁ አባት ድምፁን ከፍ አድርጎ « ቤቶች እንደምን አደራችሁ ? » ይላል ። የልጅቱ አባትም ከቤት ውስጥ ሆኖ « እግዚአብሔር ይመስገን »ደህና ሲል ይመልሳል ። ከዚያም ወደ እንግዶቹ ወጣ ይልና የልጁ አባት የሚቀመጥበትን የእንሰት ቅጠል ቆርጠው እንዲሰጡት ያደርግና ራሱም ይቀመጣል የልጁ አባት፡ ንግግር በመጀመር « ልጅህን ለልጄ እንድትሰጠኝ መጥቻለሁ » ይለዋል ። እርሱም ይመልስና « ልጄ ገና ህፃን ናት ፣ ለጋብቻ አልደረሰችም» ሲል ይመልሳል የልጁ አባት ቀጠል ያደርግና « እኔ አሳድጋታለሁ » ይላል። እንዲያውም ለደንቡ ያህል እንጂ ባንድ ጊዜ እሺ ማለት ባህል ስላልሆነ የልጅትዋ አባት የልጁን አባት ጥያቄ ችላ ብሎ በእምቢታ ይሸኘዋል ። የልጁ አባት በዚህ ሁኔታ እየተመለሰ በሦስተኛው ጊዜ የልጅቱን አባት « ወፍ ለእኔ የሰጠኝን ልጅ አትከልክለኝ ስጠኝ » በማለት አሁንም ይማጠነዋል ። ሆኖም አሁንም ሳይሳካለት ይመለሳል ። ለአራተኛ ጊዜ ይሄድና ይጠይቃል ይህኔ የልጅቱ አባት ለልጁ አባት « ልጅ ትዋ ልጅህ ናት ። ያንተ ልጅም ልጄ ነው » በማለት እሺታውን ያበስርለታል ። በደስታ ካስከተላቸው ሽማግሎች ጋር ወደ ቤቱ ያመራል ። ሰንበት ይልና እንደገና ወደ ልጅትዋ ቤት ይመጣል ። እንደደረሰም የልጅትዋ ቤተሰብ ያዘጋጁትን የተቆላ ቡና ከቆሎና ከማር ጋር አንድነት በእንሰት ቅጠል ሁለት ጥቅል አስረው ይሰጡታል ። ይህንም ይዞ ሲሄድ በመንገድ ላይ ለሚያጋጥመው ሰው ሁሉ እየቆነጠረ ባፋቸው ያደርግላቸዋል ። እነርሱም የምግቡን ትርጉም ስለሚያውቁት «ሙሽሮቹ ይውለዱ ይክበዱ » በማለት ይመርቋቸዋል። ከቤቱ ሲደርስም በቤት ላሉት ሁሉ ያከፋፍላቸዋል ። የምግቡ ምሳሌ ቡናው የተቆላው እህል ማሩ፣ ከአበቦች ከአበባም በኋላ ከፍሬ የተገኙ ስለሆኑ ፡ ምግቡ ካበባዎች እንደተገኘ ሁሉ ሙሽሮችም አብበው ያፍሩ ለማለት ታስቦ የተደረገ ነው ። ከዚህ በኋላ በሌላ ጊዜ ወጣቶች የሚጋቡበት ቀን ቀጠሮ ይደረጋል ።

የጋብቻው ቀን ቀጠሮ በሚደርስበት ዕለት ሙሽራው ሙሽሪትን ለማምጣት አይሄድም ቤት ይቆያል ። የሚሄዱት አባቱ ሚዜዎችና አጃቢ ጓደኞቹ ናቸው እነርሱም ተጉዘው ሙሽሪት አጥር ግቢ ሲደርሱ ይቆማሉ። በዚህን ጊዜ የሙሽራዋ እህቶችና ወንድሞች አጅበው ይዘዋት ይመጣሉ። ከዚያም የሙሽራው ወንድምና ሚዜው ሣር ይነጩና ለሙሽሪት እኅትና ወንድም ይሰጣሉ እነዚህ ወደ ቤት ሲመለሱ እነዚያኞቹ ሙሽሪዋን አጅበው እየዘፈኑ ይዘው ይሄዱና ከሰፈር ሲደርሱ ከሙሽራው ጋር ከተዘጋጀው ጫጉላ ያስገቡዋቸዋል ፡ ሙሽሮችም ከሚዜዎቻቸው ጋር እንጂ ከሌላ ሰው ጋር ሳይገናኙ ለአራት ቀናት ይቆያሉ ቀጥሎ አባትና እናት የቤተ ዘመዱ የመተዋወቂያ ድግስ ያዘጋጁና ሙሽሮችን ይጠራሉ ሙሽሮቹ ከመምጣታቸው በፊት ቤተ ዘመዱ ተራውን ይቀመጣል ሙሽሮቹ በአንባሮቻቸው ወንዶቹ በጣታቸው ቀለበት ዓይናቸውን እንደማሸት እያደረጉና ውለዱ ክበዱ በማለት እየመረቀ ይቀበሉአቸዋል ከዚያም ለሙሽሮቹ ከብት ገንዘብ ሌላም ሽልማት ይሰጡአቸዋል በዚህ ሁኔታ ሙሽሮቹ ተድላና ደስታ ሳይለያቸው ለስምንት ወራት ከቆዩ በኋላ ትዳራቸውን ማቋቋም ይጀምራሉ

## የጌዲኦ ብሔረሰብ ባህላዊ በዓልና ጨዋታ

በጌዲኦ ብሔረሰብ ዘንድ የገናና የመስቀል በዓላት ዝነኛ ሁነው ሲከበሩ ቆይተዋል ። እነዚህ በዓላት በዓመት አንዴ የሚመጡ በመሆናቸው የአካባቢው ሕዝብ ተሰብስበው ከብት አርደው ሥጋውን በመጥበስ አዲሱ ዘመን የመከርና የሰላም እንዲሆንላቸው እየተመኙ ልዩ ልዩ ዘፈኖችን እየተጫወቱ ይበላሉ ይጠጣሉ ። ከነዚህ በዓላት ሌላ ቄጠላ የተባለ በዓመት ሦስት ጊዜ የሚያከብረው በዓል አለ ። ይህ በዓል የሚከበረ ው በሦስት ምክንያቶች ነው ።

1ኛው ዝናብ ሣይጥል ሲዘገይ

2ኛው በማሣ ላይ ያለ እህል ጎተራ ሲገባ እንዲበረክት

3ኛ በሽታ ቸነፈር በአገር ላይ ሲመጣ እንዲወገድ ነው ።

እንግዲህ በዓሉ በሚከበርበት ዋዜማ እለት ከምሽቱ ላይ ሽማግሌዎች ይሰበ

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው
መፍትሔ የ .ሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ
ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ


ለትንሣኤ መጽሔት ምን እንርዳዎ ዓ
ምድ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስ ለዓለም ቤዛ ሲሆን በቀራንዮ ተራ
ራ በመስቀል ላይ ቅዱስ ደሙን አፍሶ
የኃጢአትን ሥራ በመስቀሉ ጠፍሮ ማ
ስወገዱ ይታወቃል ።

ይሁን እንጂ መድኀኒታቸውን የጠ
ሉ የደህንነት ቀናቸውንም ያልተረዱ
አይሁድ ጌታችንን በምቀኝነት እንደሰ
ቀሉት ሁሉ አሁንም ከምቀኝነት አ ልቦ
ዘኑምና መስቀሉን የጥራጊ መጣያ አድ
ርገው ቀብረውት እንደነበረ ታሪክ ያስ
ረዳል ። ግን ለክፉ የሚቀኑ እንዳሉ ሁሉ
ለበጐ ነገርም የሚቀኑ ስለማይታጡ እ
ሌኒ ንግሥት የጌታችንን መስቀል ከተ
ቀበረበት አስወጥታ የግማደ መስቀሉ
በተለይ የቀኙ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ
በግሸን አንባ እንዳረፈና ከዚያን ጊዜ ጀ
ምሮ ብዙ በሽተኞችን እንደፈወሰ ሙ
ታንን እንዳስነሣ ሲታወቅ ከብዙ ዓመ
ታት በኋላ ግን መስቀሉ በዚሁ በግሸን
እንደተቀበረ ይነገራል ።

ታዲያ ፈውስ የሚሰጥ ሙታንን የሚ
ያስነሣ መድኃኒት መስቀል ለምን ተቀ
በረ? አሁንስ ከተቀበረበት እንዲወጣ
ለምን ጥረት አልተደረገም? መልሱን
በናፍቆት እጠባበቃለሁ ፣ እንዲሁም
ስለመስቀል ታሪክ በዚሁ አጋጣሚ ብ
ታስረዱኝ ደስ ይለኛል ።

የዓምድህ ተከታታይ ኃይለ መስቀል
ኃይሏ ኢየሱስ ከአዲስ አበባ

ኃይለመስቀል ኃይለ ኢየሱስ ስለአ
አቀረቡት ጥያቄ እጅግ እናመሰግናለን።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስ
ቀል ሙታንን ሲያስነሣ ፣ በሽተኞ
ችን ሲፈውስ ፣ በመታየቱ አይሁድ
አሁንም ለቅንአት አያርፉምና ይህ መ
ስቀል በሚሠራው ገቢረ ተአምራት ስ
ለተዘበተባቸው ይህንን ቅዱስ መስቀል
ለማጥፋት ተማከሩ ።

ስለዚህም ሕዝቡን አስተባብረው መ
ስቀሉ እንዲቀበርና እንዲጠፋ ወሰኑ
ስለዚህም ታሪኩን እንደሚከተለው እ
ናቀርባለን ።

የታላቁ ቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥ
ት እሌኒ በቢታንያ አውራጃ በሚገኘው
ዲሬፓ በተባለው ሀገር ከአንዲት ድሀ
ቤት በ247 ዓ.ም. ተወለደች ። በተወለ
ደች በ23 ዓመቷም የቆስጠንጢኖስን
አባት ቁንስጣን አግብታ ከ247 ዓመት
በኋላ የምሥራቅና የምዕራብ የክርስት
ና ኃይማኖት ጠባቂ የሆነውን የክርስ
ቲያኖች ደም ከመፍሰስ እንዲቆም ያደ
ረገውን ቆስጠንጢኖስን ወለደች
ነገር ግን ቁንስጣ በዲዮቅልጥያኖስ
አጋዥነት የቄሣርነት ማዕረግ ባገኘ
ጊዜ የሕግ ሚስቱን እሌኒን ፈትቶ የን
ጉሡን የመክስምያኖስን ዘመድ እንዲ
ያገባ ልጁንም ቆስጠንጢኖስንመያዣ
እንዲሰጥ ተገደደ ።

በዚህ ጊዜ ሚስቱ እሌኒን
እና ልጁንም ቆስጠንጢኖስን
ከንጉሡ ካስቀመጠ በኋላ የተሰጠችው
ን አዲስ ሚስት አግብቶ መኖር ጀመረ።
እሌኒ በዚህ ጊዜ በምግባር ፣ በሃይማኖ
ት አጌጠች ። በክርስቲያናዊ አስተዳደ
ግ ያደገች ቅዱሳት መጻሕፍትንም እየ
መረመረች የተረዳች በመስቀል ፍቅር
ልቦናዋ የተነደፈ ፣ በጣም ከፍ ያለ ክር
ስቲያናዊ መንፈስ የነበራት ስለነበረች
ስለመስቀል ነገር ዘወትር ታሰላስል ነ
በር ። ከጊዜ በኋላ ክርስቲያኖች በሰማ
ዕ ትነት እንደሚሞቱ ስለምትሰማ በ
ጆሮዋ የሰማችውን በዓይኗ ለማየት ባይ
ገጥማትም እንደነሱ ስለክርስቶስ ፍቅ
ር ለመሞት ትመኝ ነበር ።

እሌኒ በ327 ዓ.ም. ወደኢየሩሳሌም
ሄዳ በዚያ መኖር ጀመረች ።ኢየሩሳሌ
ም በደረሰች ጊዜ የጌታችን የኢየሱስ ክ
ርስቶስን መቃብር የሚያሳያት አጥታ
ብዙ ከተጉላላች በኋላ ይሁዳ የሚባል
አይሁዳዊ ቦታውን አሳይቷት ብታስቆ
ፍር ሶስት መስቀሎች በአንድነት ተቀ
ብረው አገኘች ።

እነዚህም ሶስት መስቀሎች አንደኛ
ው ጌታ የተሰቀለበት መስቀል ሲሆን
ሁለቱ ግን የሁለቱ ወንበዴዎች ነበሩ።
ቢሆንም ጌታ የተሰቀለበት መስቀል
ከሶስቱ የትኛው እንደሆነ ለመለየት ተ
ቸግራ ሳለ ወዲያው አንድ ሰው ሞቶ
ስለመጣ ሬሳውን አሳረፉ መስቀሎቹ
ተራ በተራ እየቀረቡ በሙቱ ላይ ሲያ
ርፉ የጌታ መስቀል ባረፈ ጊዜ የሞተው
ሰው ተነስቶ ስለ ክርስቶስ መስክሮአል
ይህ በአንደኛው በኩል ያለው ታሪክ
ነው ።



ሁለተኛ አስተያየት ደግሞ እሌኒ ኢ
የሩሳሌም በደረሰች ጊዜ መስቀሉ የተቀ
በረበትን ቦታ አናሳያት ብለው በጣም
አስቸግረዋት ነበር ። እነርሱ ግን መስ
ቀሉን ቀብረውት በላዩ ላይ ቆሻሻ እን
ዲጣልበት አድርገው ከብዙ ጊዜ በኋላ
እንደ ትንሽ ድብ ተራራ ሆኖ ነበር ።
አይሁድን ለምና አሁንም ከላይ ስሙ
የተጠራውአይሁዳዊይሁዳስለአሳያት
ከዚያ ቦታ ላይ ብዙ እጣን ሰብስባ ዕጣ
ኑን አቃጠለች ። የዕጣኑም ጢስ ወደ
ሰማይ ከወጣ በኋላ ተመልሶ መስቀሉ
ካለበት ቦታ ስለአረፈ ብታስቆፍረው
ሶስት መስቀሎች አገኘች ። እነዚህን
ም ሶስት መስቀሎች ከላይ እንደተጠቀ
ሰው ከሙት ላይ ስታደርጋቸው የጌታ
መስቀልሙቱን ስለአስነሳየክርስቶስመ
ስቀል እንደሆነ አውቃ አከበረችው በ
ክብርም አስቀመጠችው ።

በኋላ ግን ክርስቲያኖች ስለመስቀሉ
ክብር ስለ መስቀሉ ገናናነት በዓለም
ዙሪያ ሲሰሙ ክርስቶስ በመስቀል ተሰ
ቅሎ ደሙን ያፈሰሰው ለመላው ዓለም
በመሆኑ መስቀሉ ተከፋፍሎ ለዓለም
መዳረስ ያለበት መሆኑን በማመን መስ
ቀሉ ወደየክፍለ ዓለማት ተከፋፈለ ፤
ከነዚህም አንዱዋ ዕድለኛ ኢትዮጵያ
በመሆኑዋ ግማደ መስቀሉ በአፄ ዳዊት
ና ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት
ወደኢትዮጵያ መጣ ከዚያም በልዩ ልዩ
የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት ሲዘዋወር
ከቆየ በኋላ በወሎ ክፍለ ሀገር በአንባሰ
ል አውራጃ ግሼን አንባ ሄዶ አረፈ ።
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መስቀሉ ልዩ ልዩ
ገቢረ ተአምራት ሲያደርግና በሽተኞች
ን ሲፈውስ ሙታንን ሲያስነሳ ለብዙ
ዓመታት ከቆየ በኋላ ባልታወቀ ጊዜ በ
ምን ምክንያት እንደሆነ ሳይታወቅ ተቀ
በረ ፣ ለምን ግን እንደቀበረው ግን አል
ታወቀም ።

ከሁሉም የሚያሳዝነው ግን መስቀሉ
ከተቀበረበት እንዲወጣ ጥረት ያደረገ
ሰው አለመኖሩ ነው ታዲያ ግማደ መስ
ቀሉ ወደኢትዮጵያ መጥቶ ከተቀበረ
ባይመጣ አይሻልም ነበርን? የሚሉ አን
ዳንድ አስተዋዮች ባይጠፉም ከተቀበ
ረበት እንዲወጣ ጥረት ያደረገ ግን እስ
ከአሁን የለምና ለወደፊቱ ጥረት ቢ
ደረግ መልካም ይመስለኛል ።

## የጌዲኦ ብሔረሰብ ....

ከገጽ ፱ የዞረ

ሰቡና ጥሩምባ እንዲነፋ ያዛሉ ።
ሕዝቡ ይሰበሰባል ፡ ሥነ ሥርዓቱ ሲጀ
መር የመለማመጃያው በግ መስዋዕት
ሆኖ ይቀርባል ። ባህላዊ የዘፈን ዓይነ
ቶች ይሰማሉ ። በዓሉ በሚቀጥለው ቀን
ይካሄዳል ።

ስለባህል ጨዋታ ካነሳን ዘንድ የ
ጌዲኦ ብሔረሰብ በዳንኪራ ጨዋታ የተ
መሰከረለት ነው። በዓል በሆነ ቁጥር ጎረ
ምሶችና ኮረዶች ተጠራርተው ይመጡና
ያሸበሽባሉ ዳንኪራ ይመታሉ አረጋው
ያን ወንዶችና ሴቶችም የነብር ለምድና
ካባ ደርበው ጠመንጃ ፣ ጦር ጋሻ ይዘው
እየተቀባበሉና እያኮበኮቡ የባህል ጨዋ
ታቸውን ለተመልካች ያቀርባሉ ዳንኪራ
ው ወይም ሽብሸባው በከበሮ በዲቤ ፣ እ
ንደ እንቢልታ በሚነፋ የሙዚቃ መሣሪ
ያዎችና በጡሩምባ ይታጀባል ።

ብሔረሰቡ የሚዝናናባቸው ልዩ ልዩ
ባህላዊ ስፖርቶች አሉት ። ለምሳሌም
ያህል ወጣቶቹ በጦር ውርወራ በዘንግ
ዱላማ ፣ በሩጫ ፣ በትግልና በዝላይ ስፖ
ርቶች ይሳተፋሉ ይወዳደራሉ ። ሽማ
ግሌዎችም ለነዚህ ስፖርቶች ደንብና ሥ
ርዓት በማውጣት በሥፍራው ተገኝተው
ተሳታፊዎችን ያበረታታሉ ።

### ሰው ሲሞት የቀብሩና የኀዘኑ ሁኔታ

በቀድሞው ባህልና ወግ መሠረት ሲ
ታይ ሰው በሞተ ቁጥር በብሔረሰቡ ዘ
ንድ ኀዘን ይጠነክራል አንድ ሰው ሲሞት
እጅ እግሩ ተጣጥፎ ኩርምት ይደረግና
ይገነዛል ። ከዚያም የመቅበሪያው ጉድ
ጓድ ወደታች ጥልቀቱ ስድስት ክንድ
ወይም ሁለት ሜትር ፣ ወደጎን ደግሞ
ሦስት ክንድ ወይም አንድ ሜትር ተደ
ርጎ ከተቆፈረ በኋላ እሬሳው ገብቶ ወደ
ጎን ከተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ይቀበ
ራል ። ሟቹ ባላባት ወይም የታወቀ ጀ
ግና እንዲሁም አዳኝ ከሆነ ሴቶች ፊታ
ቸውን እየነጩ ወንዶች ደግሞ ራሳቸውን
በጦር እያቆሰሉና ድንጋይ ላይ እየወደቁ
በጠለቀ ኀዘን ሬሳውን ይሸኙታል ። የኋ
ላ ኋላ ግን ይህ ድርጊት አግባብ አለመ
ሆኑ ታወቀ ሰው ሲሞት በቁመቱ ልክ
እንዲገነዝና እንዲቀበር ሲደረግ በኀዘን
ም በኩል አካልን መጉዳት ቀርቶ አልቃሾ
ቹ በከበሮ ታጅበው እንዲያለቅሱ ሆኖ
አል ። እዚህ ላይ ሟቹ ባላባት ጀግና ወይ
ም የታወቀ አዳኝ ከሆነ ከተቀበረ በኋላ
ለሰባት ቀን ከእኩለ ቀን በኋላ ይለቀስለ
ታል ። ነገር ግን ሟቹ ተራ ሰው ሲሆን
ይህ ኀዘን ለሦስት ቀን ብቻ ይደረግለ
ታል ። ከዚህ ቀጥሎ ለተዝካር ድግስ ይዘ
ጋጅና የቅርብና የሩቅ ዘመዶች ተጠርተ
ው ይመገባሉ ።

### የጌዲኦ ብሔረሰብ በባህል ዘመቻው

የጌዲኦ ብሔረሰብ በመላው ኢትዮጵ
ያእንደሚገኙልዩልዩብሔረሰቦችሁሉ፡
በእኗኗሩ ውስጥ ሠርገው በመግባት ጠ
ቃሚ ባህሎቹን የበከሉትን አጉል ልም
ዶች ለማስወገድ በጥረት ላይ ይገኛሉ ።
በቤተሰብ አቋም ፡ በጋብቻ ፡ በኀዘን ወ
ቅቶችሲፈጸሙየቆዩትንኋላቀርናጎታች
ባህሎችን ታግሎ ለማስወገድ የሚቻለ
ው በትምህርት ከሚገኝ ንቃተ ህሊና መ
ሆኑን በመገንዘብ የመሠረተ ትምህርቱ
ን ዘመቻ በንቁስ ወጥቶ በደስታ ተያይዞ
ታል። በትምህርትና በባህል ተሃድሶው
መስክ ከጎኑ ሁነው መመሪያ ከሚሰጡት
ባለሙያዎች ጋር በቅርብ በመመካከር
ለታሪክ ሊያቆያቸው የሚገቡትን የባህ
ሉን ዘርፎች በመገንባት ላይ ይገኛል ።




www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## የችቦና የደመራ መነሻ

የችቦና የደመራ መነሻ ታሪክ እንዴት እንደሆነ ወደኋላ መለስ ብለን ታሪክን ስንመረምርና አንዳንድ ሊቃውንትን አነጋግረን ያገኘናቸውን ጥቆማዎች ለአንባቢያን በመጠኑ ለመግለጽ እንሞክራለን ።

ታሪኩም እንዲህ ነው የጥንቱ ኅብረተሰብ በተለይ ችቦን ይጠቀምበት የነበረው 1ኛ በዚያን ጊዜ እንደአሁኑ ዘመን ስልክ ፡ ቴሌግራም ፣ ወይም ሬድዮ ስላልነበረ በጊዜው የሚፈጸመው የነበረው የደስታና የድል የምሥራች በፍጥነት ለማዳረስ ከተራራ ላይ ሆነው በችቦ መልክ መብራት ያበራሉ በየተራራውም ወታደሮች ስለሚቀመጡ እነዚያ ደግሞ ሌሎቹን እየተከተሉ ያበራሉ በዚህ ዓይነት እየተቀባበሉ በመብራት ምልክት ደስታቸውን ለተቀሩት ክፍላተ ሀገራት እንዲዳረስ ያደርጉ ነበር

2ኛ በዚያን ጊዜ የነበሩት ኅብረተሰቦች የጣኦታቸውን በዓል የሚቀበሉት በዘንባባ ዝንጣፊና በችቦ እንደነበር ይናገራሉ ። ባጠቃላይ ግን ችቦ የሚበራው ለደስታ መግለጫ እንጂ ለሃዘን እንደማይበራ ይተረካል ።

የደመራው ታሪክ ደግሞ ከዚህ ለየት ባለ ሁኔታ መጻሕፍት ሲያስረዱ ብዙ በሽተኞችን የፈወሰ ብዙ ሙታንን ያስነሣ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል አይሁድ እንዲጠፋ አድርገውት ነበርና ንግሥት እሌኒ የጠፋውን የክርስቶስን መስቀል ለማግኘት ፍለጋዋን ከመጀመሯ በፊት በመጀመሪያ ምልክት ለማግኘት ስትል መስከረም 17 ቀን እርጥብ እንጨት አስቆርጣ ደመራ አስደምራ ካህናቱን ካጸለየች በኋላ በእሳት እንዲያያዝ አደረገች የደመራው/የዕጣኑ/ ጢስም መስቀሉ ወደተቀበረበት ቦታ ስላረፈ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቁፋሮው ፍለጋ እስከ መጋቢት 10 ቀን ቀጥሎ በመጋቢት 10 ቀን 327 ዓ.ም. የጠፋው መስቀል እንደተገኘ ያስረዳናል ።

ችቦ እንግዲህ የመስቀል ዕለት መበራት የተጀመረበት ዋናው ምክንያት ከላይ እንደገለጽነውና የቤተ ክርስቲያን ታሪክም እንደሚያስረዳው ንግሥት እሌኒ መስቀሉ በተገኘ ጊዜ ደስታዋን ለልጅዋ ለቆስጠንጢኖስ ለመግለጽ ጊዜው በሚፈቅደው የመገናኛ ዘዴ ሕዝቡ በየተራራው ችቦ እያበራ እንዲያስተላልፍ ስላደረገች ሳይዘገይ በችቦው ብርሃን አማካይነት የምሥራቹ ለልጅዋ ስለደረሰው በዚህ ምክንያት ተለመደ ይላል ።

ይኸው ታሪክ ሐተታውን በመቀጠል ቆስጠንጢኖስ የሠራውን መቅደስ በፐርሺያ ዛሬ ኢራን ተብሎ በሚጠራው አገር የነበረው ገገር ንዋየ ቅድሳቱን ና ዕሌኒ አስቆፍራ ያስወጣችውን መስቀል ክርስቲያኖችንም ጭምር ማርኮ ከላይ ወደተጠቀሰው አገር ወስዶአቸ ነበር ። የቁስጥንጥንያ ንጉሥ614ዓ.ም. ው ነበር።የቁስጥንጥንያ ንጉሥ 614 ዓ. ም. ሕርቃል የፋርስ ንጉሥ የማረካቸውን ክርስቲያኖች ንዋየ ቅድሳትና መስቀሉንም ጭምር እንዲመልስ ጠይቆት በ629 ዓ.ም. ጦርነቱ ቀርቶ በሙሉ ተስማምተው የማረከውን ዕቃ ፣ ሥዕል ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል ለሕርቃል መለሰለት በዚሁ ጊዜ መስከረም 17 ቀን የዋዜማው ዕለት ማታ የቁስጥንጥንያ ንጉሥ ሕርቃል ዕቃውንና መስቀሉን ወደ ኢየሩሳሌም ይዞ ሲገባ በኢየሩሳሌም ከተማ ዳር የነበሩት ቃፊሮችና የከተማው ሕዝብ ችቦ እያበሩ ተቀበሉት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መስከረም 17 ቀን በየዓመቱ እንዲከበርና ችቦም እንዲያበራ ሆነ ይላል ። ይህም መልካም ተግባር በመሆኑ እየተለመደ ወደሀገራችን ደርሶ ቤተ ክርስቲያኖችንም ይህ መንፈሳዊ ቅርስና ከታሪክም ሲያያዝ የመጣ በመሆኑ በያመቱ መስከረም 17 ቀን በደማቅ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ።

በበዓሉ ዋዜማም ደመራ ተደምሮ ካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ስብሐተ እግዚአብሔር ያደርሳሉ ጸሎት ይጸልያሉ ምህላ ያደርጋሉ በዚህም ዕለት ብዙ ሕዝብ በበዓሉ ሥፍራ ይገኛል በዚህን ጊዜ ደመራው ተባርኮ ከተቀጣጠለ በኋላ ሕዝቡ ችቦውን አቀጣጥሎ ደስታውን በሆታና በዕልልታ ያበሥራል ።

.በዚህም ምሽት ሁሉም በየቤቱ በየደጁ ከዘመድና ከጐረቤት ጋር በመተባበር ችቦ ያበራል በአንዳንድ ጐሳም ለብዙ ጊዜ ተለያይተው የነበሩ ቤተሰቦች ለመስቀል በዓል ይገናኛሉ ። ይህም የመስቀል በዓል በደማቅ ሥነ ሥርዓት የሚከበረው በተለይ በጉራጌ፣በኦሮሞና በትግራይ ብሔረሰቦች ዘንድ ነው ይባላል።

እንግዲህ ደመራው የንግሥት እሌኒን ደመራ ምሳሌ የያዘ ሲሆን በሌላ መን

---

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# የአክሱም ቅ/ያሬድ አዳሪ ት/ቤት አንድ ድጓ በርዳታ አገኘ



መልአከ ፀሐይ ገ መድኅን ለመምህር ዘኬዎስ መጽሐፈ ድጓውን ሲያስረክቡ

ፍቅረ እግዚአብሔር ያደረባቸው መንፈሳዊ ቅንዓት ያላቸው ክርስቲያኖች እንደየስሜታቸውና እንደየብፅዓታቸው ስዕለታቸው ልዩ ልዩ ንዋየ ቅድሳት ይሰጡ እንደነበር አሁንም በመስጠት ላይ እንደሚገኙ ለማንም ግልጽ ነው በየአብያተ ክርስቲያናቱ በየገዳማቱ የሚገኙት አስደናቂ ቅርሶች ሥዕሎች ወዘተ ሲነበቡ ዝመስቀል ዝሥዕል ዘ ወሀቦ እገ ሌ ለታቦተ እገሌ ከመ ይኩኖ መርሐ ለመንግሥተ ሰማያት ይላል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ለማንኛውም ክርስቲያ ምዕመናን ለማንኛውም ክርስቲያናዊ ሥራ የተዘጋጁ ናቸው የምናያቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የግል ቤቱን ከምሥራ ቤተ ክርስቲያን ልሥራ እያሉ በገንዘባቸውና በጉልበታቸው ያሰሯቸው ናቸው ። አሁንም በየአካባቢው አስደናቂ አብያተ ክርስቲያናት እየተሰሩ ናቸው ሥጦታም ከላይ እንደገለጽነው እንደየስሜቱ እንደየብፅዓቱና እንደየሥዕለቱ ይሆናል ለአሁኑ ጽሑፋችን መነሻው መልአከ ፀሐይ ገ መድህን ደስታ የተባሉ በጎ አድራጊ ለአክሱም ቅ/ያሬድ መ.አዳሪ ት/ቤት አንድ መጽሐፈ ድጓ በእርዳታ ሰጥተዋል ። እኚሁ በጎአድራጊ ሰው በኅዳር 24 ቀን 73 ዓ.ም አቶ ፀጋዬ በርሄ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ.ተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ኀ ቤኤ ዋና ጸሐፊ የቅዱስ ያሬድን ት/ቤት በጎበኙበት ወቅት እንደአጋጣሚ መልአከፀሐይ ገ መድህን የጉብኝቱ ተካፋይ ሁነው ነበር በዚህ ጊዜ የቅዱስ ያሬድ ተማሪዎች የተለያየ መንፈሣዊ ትምህርት ይማሩ ነበር እርሱም ከድጓ ጀምሮ እስከ መዝገበ ቅዳሴ ነበር እንደዚሁም በኅብረት ሆነው መንፈሳዊ መዝሙር ዘምረው ነበር ። በዚህ ጊዜ መልአከ ፀሐይ ከደስታቸው ብዛት የተነሣ አንድ መጽሐፈ ድጓ እስጣለሁ ብለው በአቶ ፀጋዬ በርሄና በመምሕራን እንደዚሁም ለወደፊቱ የቤተክርስቲያኒቱ ተረካቢዎች በሆኑት ተማሪዎች ፊት ቃል ሲገቡ ተማሪዎቹ የተለየ ደስታ ተሰምቷቸዋል ሞራላቸው ከፍ ብለዋልእኚህ መንፈሳዊ ቅንዓት ያላቸው ሰው መጽሐፈ ድጓውን ባለፈው ሆሣዕና ለት ቤቱ አበርክተዋል መጽሐፈ ድጓውን የተረከቡት ከአሁን የድጓምሩቃን አንዱ የኔታ ዘኪዎስ አማረ ናቸው በርክብክቡ ሥነ ሥርዓት የድጓ ምሩቃንና ሌሎች ተማሪዎች ተገኝተዋል እኚህ በጎ አድራጊ ለዓድዋ ፊለገ ሕይወትም ሕጻናት ማሳደጊያ ድርጅት በርከት ያለ ውዳሴ ማርያም በዕርዳታ ሰጥተዋል ወደፊትም ሌሎችን በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር እስከ መጨረሻ ድረስ የሚተባበሩን መሆናቸውን ቃል ገብተውልናል እኛም አሳባቸውን ሁሉ እንዲያስፈጽማቸው ፈጣሪያችንን እንለምንላቸዋለን እናመሰግናቸዋለን ።

የቀደሙ አባቶቻችን ቅድስት ቤተክርስቲያንን ከነሙሉ ሥርትዋና ቅርሶችዋ አስረክበውናል እኛም ለመጪው ትውልድ የአባቶቻችን ይህ ነው የኛ ደግሞ እነሆ ብለን ለማስረከብ እንችል ዘንድ በያለንበት አካባቢ መንፈሳዊያን አዳሪ ት ቤቶች ያሉትን ተማሪዎች እንርዳቸው እንከባከባቸው በአሁኑ ጊዜ መንፈሳዊ ተማሪ ከፍተኛ ቅርስነው ያሉን አበው መምህራን ወደዱም ጠሉም ተመቻቸው ምክፋቸውም ቤተክርስቲያቱን እያገለገሉ ናቸው ችግሩ የሚረከባቸው ማን ይሆን ? መልሱ የሕዝበ ክርስቲያን ሲሆን ቃሉም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚማሩትን ተማሪዎች መርዳት ነው ቀድሞም ቢሆን በኢትዮጵያ ያሉትን ሊቃውንት አባት እናታቸው አሳስተማሯቸውም ያስተማሯቸው ክርስቲያኖች ሁሉ ናቸው ስለ ተማሪው ከልጁ አብልጦ ማሰብ በተለይ በሴቶች በኩል የነበረው አሁንም ያለው ክርስቲያናዊ ርህራሄ ወደር የለውም ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ን ቤተክርስቲያን የሚያሰኛት ትምህርት ነውና ሁላችንም እናስብበት ።

መ. ኃ ሚካኤል
የአዳሪ ት ቤቱ አስተዳዳሪ



www.ethiopianorthodox.org

√ ቃ/ሐ/ብ/ክርስቲያን፡ምክሩ-

# የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፡ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፥፫) ።

## ሃይማኖትና ሥነምግባር

"ከነፍስ የተለየ ሥጋ ምውት እንደ ሆነ ከበጎ ሥራ ወይም ከምግባር የተለየ እምነትም የሞተ ነው ።" (ያዕ፡2፡26።)

አንዳንድ ሊቃውንት ሃይማኖትን በፈረስ ፣ ምግባርን ደግሞ ፈረሱ በሚጐትተው ጋሪ ይመስሉታል ። ታዲያ ፈረሱ በሚሄድበት ስፍራ ሁሉ ጋሪውም ተከትሎት እንደሚጓዝ ሃይማኖትም ባለበት ቦታ ሁሉ መልካም ሥነ ምግባር ተሳቢ ሆኖ ይገኛል ።

ሌሎች ሊቃውንት ደግሞ ሃይማኖትን በመሠረት ፣ ሥነ ምግባርን በጣሪያና ግድግዳ ይመስሉታል ። ይኸውም መሠረቱ ካማረ ጣሪያና ግዳድግዳው እንደማይዛባ ሃይማኖትም ካለ ዘንድ ያማረ ሥነ ምግባር በትክክል ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው ።

በመሠረቱ ሃይማኖት ያለው ሰው ራሱን ከሕግ በላይ አያደርግም ፤ የፈጣሪውን ስም በከንቱ አያነሣም ፤ እናትና አባቱን ያከብራል ፣ በሌሴት አይመሰክርም ፤ የባልንጀራውን ሀብት ንብረት አይመኝም ባልጀራውን እንደራሱ ይወዳል ። በራሱ ላይ ሊደርስበት የማይፈልገው ነገር በሌሎች ወገኖቹ ላይ እንዲደርስባቸው አይፈልግም "ሌሎች ሊያደርጉልህ የምትፈልገውን ነገር አንተም ለነርሱ አድርግላቸው" የሚለውን ወርቃዊ ሕግ መመሪያው ያደርጋል ።

እንግዲህ ሐቁ ይህ ሆኖ ሣለ እምነት ባላቸው በአንዳንድ ግለሰቦች የሚፈጸም ስሕተት ቢኖር የሃይማኖት ማጥበቂያ ቡሎን ያስፈልጋል ። እርሱም ትክክለኛውን የሃይማኖት መመሪያ ትምህርት ማግኘት ነው ። ፈላስፋው ፕላቶን ሰው ትክክለኛውን ትምህርት ካገኘ እግዚአብሔርን የሚመስል ለስላሳ (ኖብል) ይሆናል" ሲል የተናገረውም ስለዚሁ ነበር ።

ባጠቃላይ አገላለጥ መልካም ምግባር ማለት ሊሠሩት የሚገባውን መልካም ነገር ሁሉ መፈጸም ፣ ሊሠሩት የማይገባውን ክፉ ነገር ሁሉ ደግሞ መሸሽ ማለት ነው እንዲያውስ ብላታ ወ/ጊዮርጊስ እንደሚሉት "ለክፉ ሥራ ሁሉ ቦይ አትሁን" "በግብረ ገብነት ያልታሸ ሰውነትና ያልተለፋ ቆዳ ሁለቱ አንድ ናቸው"

እርሱንም የዓለም መድኅን ክርስቶስ ባስተማረው ወንጌል የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያንን ትምህርት "እርሾ" ብሎ ሠይሞታል ።

(ማቴ. 16 ፣ 12)

በሉቃስ 17 ፣ 10 "እንዲሁም እናንተ የታዘዛችሁትን ሁሉ ካደረጋችሁ በኋላ እኛ ምንም የማንጠቅም አገልጋዮች ነን ፣ ልናደርግ የሚገባንን ብቻ አድርገናል በሉ" ሲል ሰውን በሚፈጽመው በጎ ምግባር ሁሉ ትምክሕትና ትዕቢት አድሮበት ለይስሙላ ለታይታ ሰዎች ተመልክተው ያመሰግኑት ዘንድ ከንቱ ውዳሴ በመሻት የሚፈጽመው የግብዝነት አሠራር ዋጋ እንዳያሳጣው ደጋግሞ አስጠንቅቋል ።

ይህም ያለ ምክንያት አይደለም ። ሐዋርያው ጳውሎስ እንኳ በግልጥ ሲናገር "በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ" በማለት ራሱን በሌሎች አማኞች ቦታ አድርጎ በውክልና መልክ የተናገረውን ቃል እናስታውስ ። ባጭሩ ይህ አባባል የሚያስገነዝበን ቁም ነገር ሰው ሁሉ በተፈጥሮው ደካማነት ብቻ አንድ ጊዜ ወደ ጽድቅ አንድ ጊዜ ደግሞ ወደኃጢአት በማዘንበል ሲወድቅ ሲነሣ የሚኖር ፍጡር መሆኑን ነው ፤ እንግዲያውስ ሃይማኖቱን መሠረት አድርጎ ከሚከተለው መልካም ሥነ ምግባር በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት እንዲጨመርለት ራሱን ዝቅ አድርጎ በጸሎት መለመን ይገባዋል ፤ ይኸውም የሚቻለውን ያህል ምግባር ትሩፋት ለመሥራት እየሞከረ እንጂ "በጸጋው ብቻ ስለምድን ምግባር አያስፈልገኝም ለማለት አይችልም ። በዕርግጥ አንድ ደራሲ እንደሚል "ከሰል ብትፈጭ ነጭ ዱቄት እንደማይወጣው ሰው በተባለ ፍጥረት ሁሉ እንከንና ጉድለት ስለማይታጣ ሙሉ በሙሉ ፍጹምነት አይገኝም ። ፀሐይ በምትበራበት ስፍራ ሁሉ ጥላ እንደሚገኝ እንዲሁም የሰው በጎነት ከክፋት ጋር ተጣምሮ ይገኛል መልካም የወይን ጠጅ እንኳ አተላ አለው ተብሏልና ነው ። ይሁን እንጂ የዚህ ሁሉ ጉድለት መኖር አንድን አማኝ ከእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት ውጭ ሊያደርገው አልቻለም ። የሰው ዘር በደል በበዛ መጠን የእግዚየአብሔርም ምሕረት እጅግ የበዛ በመሆኑ አማኝ ሁሉ እንደሃይማኖቱ ጽናት ብቻ ሳይሆን እንደመልካም ሥራውም መጠን ዋጋ እንደሚያገኝ ተጽፎዋልና ።

እንግዲያውስ ለሰው ዘር ደህንነት ተቀዳሚው እምነት ሲሆን ተከታዩ ምግባር የሁሉም አጠናካሪ ኃይልና መደምደሚያው ደግሞ የእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት በመሆኑ በራሱ ምግባር ብቻ ሳይታበይ የሚመካ ቢኖር በእግዚአብሔር ይመካ ።



## ለእውነት የሞተ

ስለ እውነት የታሠሩ ፣ ስለ እውነት የሞቱ ፣ የመንፈስ ጀግኖች እጅግ ብዙ ናቸው ። ከእነዚህም መካከል የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ ድልድይ የሆነው ፣ የአዲስ ዘመን መለወጫ በዐል እንዲሆን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የወሰነችለት ፣ በምድረ በዳ የሚጮኽ መጥምቁ ዮሐንስ ነው ።

ኢሳይያስ እንደተናገረው የአዋጅ ነጋሪ ቃልና ጩኸት " የእግዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ .... ተራራው ዝቅ ይላል ሸለቆውም ከፍ ይላል ስርጓጉጡም ሜዳ ይሆናል » የሚል ነበር ። ትንቢተ ኢሳይያስ ምራፍ 40 ቁጥር 3-4 የዮሐንስ ወንጌል ም . 1 ቁ . 23 ።

መጥምቁ ዮሐንስም ይህን በሚያስተምርበት ጊዜ ተራራ ያላቸው እነማን ነው?የድሆችእንባእንደክረምትጎርፍቢፈስአንድጥርኝውሃየፈሰሰየማይመስላቸውንችግረኞችተርበውናተጠምተው ፍርድ አጥተው ሲያለቅሱና ሲጮሁ የውሻ ቡችላ እንደ ጮኸ የማይቆጥሩትን ፣ ማንም ሰው በግፍ ታስሮ እየተሰቃየ ቢሞት የድመት ግልገል እንደሞተ አድርገው የማይመለከቱትን ፣ከሕዝቡም ተለይተው ሁሉ ለኔ የሚለው የስግብግብነት ጠባይ ያጠቃቸውን ሄሮድስንና ግብረ አበሮቹን ነው ።

ለምሳሌ ሕጉ እንደሚፈቅደው ከሆነ ለሕዝብ ኃላፊ ሆነው መሾም የሚገባቸው በእኩልነት የሚያምኑ ስለ እውነት በውነት የሚፈርዱ ፣ ርህራሔ ያላቸው ሠርተው የሚያሠሩ ፣ ለኔ ከማለት ይልቅ ለኛ የሚሉና፣በጠባያቸውና በሙያቸው በሕዝብ የተመሰከረላቸው ሰዎች ናቸው ። ሄሮድስና ግብራበሮቹ ግን መጥምቁ ዮሐንስእንደተናገረው ጠባያቸውን በመልካም ተግባር በሕዝብ ፍቅር ላይ መመስረታቸውን ትተው በገንዘብ ፍቅር ስለተያዙና ለግል ጥቅም ተገዢ ስለሆኑ ሕዝብን ከማገልገል ይልቅ ራሳቸውን ማገልገል መረጡ ።

ስለዚህ አንድ ሊቅ ሲናገር" ከሰዎች ሁሉ የማታዘንለት የመጨረሻ እድለቢስ ፍጡር ፣ የሌሎችን ጠቃሚ ምክርና ተግሣጽ ሳይቀበል በራሱ አሳብ የሚመራ ነው ። እንዲህ ያለውም ሰው ዓይኑን በግል ጥቅም ጋርዶ ወደ ጥፋት ከመገስገስ አያቋርጥም ፣ በውድቀቱም የሚራራለት የለም" ብሏል ። እንዳለውም ሄሮድስ በግል ጥቅም ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው ዓይኑ ስለተጋረደ ድሆች ቢያለቅሱ ፣ ፍርድ ቢጎድል ፣ አድልዎ ቢደረግ እሱና ግብራበሮቹ ከጠገቡ ሌላው ቢራብ ፣ ቢቸገር ደንታ አልነበረውም ። ቅዱስ ዮሐንስም ከጥፋቱ እንዲመለስ ፣ ንስሐ እንዲገባ ፣ ቢመክረውም ቢያስተምረውም ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው ጆሮው በነገረ ሰሪዎች ስብቅ ስለደነቆረ ፣ ትምህርቱንም ሆነ ተግሳጹን ሊሰማ አልቻለም ።

መጥምቁ ዮሐንስ ግን ለታሰሩት መፈታትን ፣ ለተጠቁትም ነጻነትን ያገኙ ዘንድ ፣ አገዛዝ ለከበዳቸው ፣ ሐዘን ለጸናባቸው ፣ ለሚያለቅሱና ተስፋ ለሚቆርጡ ሁሉ የምሥራቹን ፣ ደስታን ፣መጽናናትን ፤ ነጻነትን ፤ አዲሱን ዘመንና የመንፈስን ለውጥ የእግዚአብሔርንም ዓመት የክርስቶስን መምጣት መሰከረ።

እሱ በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል ፣ እኔ ግን በንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ ፤ ምሳርም በዛፍ ስር ተቀምጦአል የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ፣ ወደ እሳትም ይጣላል"እያለ አስተማረ ። የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ቁጥር 10-11 ።

መጥምቁ ዮሐንስም ይህንን ሁሉ ሲሰራ በሳንቲም የሚቆጠር ገንዘብ አልነበረውም።እራሱንም የሚያስጠጋበት ጎጆ እንኳን አልነበረውም ። እረዳትም አልነበረውም ። የእግዚአብሔር ኃይልና የመንፈስ ብርታት ስለነበረው ብዙ ጦር አስልፎ መዋጋት ከሚችለው ከሄሮድስ ጋር ብርቱ ተቃውሞ አደረገ ። ተቃውሞውም እንዲህ ነበር ። በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 14 ቁ 12 እንደሚነበበውና የቤተ ክርስቲያንም ታሪክ አባት አውሳብዮስ ዘቂሣርያ እንደሚያብራራው ታላቁ ሄሮድስ አራት ልጆች ነበሩት ። እሱ ከሞተ በኋላ ዮሐንስን ያስገደለው ሄሮድስ አንቲፓ፣ የቀሩትም ወንድሞቹ አባታቸው ያስተዳደረው የነበረውን አገር ለአራት ተከፋፍለው ይገዙ ጀመር ለሄሮድያዳ የመጀመሪያ ባል የነበረው ፊሊጶስ ስለሞተ የገሊላና ቤርያ ገዢ የነበረው ሄሮድስ አንቲፓ የወንድሙን የፊሊጶስን ሚስት ሊማግባት ፈለገ ። ዮሐንስም እውነተኛ ነቢይና ካህን ስለነበር ሄሮድያዳን እንድታገባት ሕግ አይፈቅድልህም ሲል ሄሮድስን በመጀመሪያ ለብቻው መከረው፣ ጋብቻውን አልተውም በማለቱ ባደባባይ ገሰጸው ። እውነት በመናገሩ ዮሐንስን አሰረው ።

የልደቱንም በዓል በሚያከብርበት ቀን የሄሮድያዳ ልጅ የእስረኛውን የዮሐንስን እራስ አስቆርጠህ በዚህ በወጭት ስጠኝ ስትል ለመነችው።ሄሮድስም የገባውን ቃል ለመለወጥ ስላልፈለገና ሄሮድያዳንና እንደሱ ግብዝ የሆኑትን ግብረ በላዎች መኳንንቶቹን ለማስደሰት ሲል አስቆርጦ ሰጣት ዮሐንስ ስለእውነት ሞተ ተቀበረ ። ሄሮድስና መኳንንቱም ለጊዜው ደስ አላቸው ።

ስለዚህ እውነት በሐሰት ርህራሄ በጭካኔ የሚለወጥበት ገበያ በሄሮድስና በግብራበሮቹ የደራ ሆነ በዚህ መጥፎ ድርጊት የሰው ሕይወት የግፍ ቁና የሚሰፈርበት ገበታ ተዘረጋ ። ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ሄሮድስ ለጠቅላላው ኅብረተሰብ የሚያበራውን መብራት አጥፍቶና ሕዝቡን በጨለማ ውስጥ ጥሎ የሚነደውንና የሚቃጠለውን ዮሐንስን ያህል ታላቅ መብራት ለአንዲት ሴት ደስታና ለጥቂት ሰዎች ፈንጠዝያ ሲል ማጥፋቱ ነው ።

ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መብራትነትና እውነተኛ መሆን ታላቁ መጽሐፍ እንዲህ ይላል" እናንተ ወደ ዮሐንስ ልካች



www.ethiopianorthodox.org

ኋል ። እርሱም ለውነት መስክሮአል። እርሱም የሚነድ የሚያበራ መብራት ነበር ። እናንተም ጥቂት ዘመን በብርሃኑ ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ” ይላል የዮሐንስ ወንጌል ም.5 ቁ.33-35 ።

እንደተባለውም እሳት ሁለት ጠባይ አለው አንደኛው የመንደድ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ብርሃን መስጠት ነው ። በመንደዱ ሙቀትን እየሰጠ ብርድን ያስወግዳል በብርሃንነቱም የተሰወረውን ሁሉ ገልጠ ያሳያል ፤ ጨለማንም ያርቃል ። ዮሐንስም የዚህ ጠባይ ስለነበረው ስለ እግዚአብሔር ስምና ክብር እንደ እሳት ይነድና ይቃጠል ነበር ። እሱም የሚመሰክረው የራሱን ብርሃንነት ሣይሆን ስለ ክርስቶስ ብርሃንነት ነበር። የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቁጥር 8 ብርሃንነቱም ወደ ራሱ ሣይሆን ወደ ክርስቶስ ነው የሚያሳየው ። በዚህ አንፃር ዮሐንስ ለራሱ ክብር ሣይሆን ስለ ክርስቶስ ክብር በሚመሰክርበት ወቅት እንደ ሻማ እየቀለጠና እንደ እሳትም እየነደደ ለሌላው የሚያበራ ብርሃን ነበር ።

ለምሳሌ አንዲት ሴት የሰራችውን ተግባር ከዚህ መጥቀስ ያሻል ሴትየዋ እመቤት ነበረች ። ባልዋ ግን ሰካራም ከመሆኑም ሌላ በውድቅት ሌሊት እየመጣ አስቸገራት ። በቤትም የኤሌክትሪክ መብራት ስላልነበራት ከእንቅልፏ ተነስታ እሳት አቀጣጥላና አንድዳ መቆየት ታላቅ ችግር ሆነባት ስለዚህ ሻማ አብርታ ትተውለት ጀመር ። አንድ ቀን ያለ ልክ ሰክሮ መጣና የሚበራው ሻማ ሁለት መስሎ ታየው ለምንድነው ሁለት መብራት የሚበራው አለና የሚያበራለትን ሻማ እፍ ብሎ አጠፋው በመጨረሻም በከባድ ጨለማ ላይ ወድቆ መብራት ሆኖ በሚያበራለት ጊዜ

እንዲህ የሚያደርገው ይህ ሰው ብቻ አይደለም ሄሮድስና ግብራበሮቹ ይህን ተግባር ፈጽመዋል ። መጥምቁ ዮሐንስ በኃጢአት ለሰከረው ዓለም የጨለማ መብራት ሆኖ በሚያበራበት ጊዜ ተቃውመውት ነበር ። እሱ ግን በዚያን ዘመን ለነበረው ለጋብቻ መፍረስ ፤ ለማህበራዊ ኑሮ መዘበራረቅ ፤ ለምዕመናን መንፈሳዊ ሕይወት አለመስተካከል በጣም ይናደድና ይቆረቆር ነበር ። ክርስቶስ “ የቤትህ ቅንአት በላኝ” ሲል እንደተናገረው ለእግዚአብሔር መንግሥት መንፈሳዊ ቅንአት ስለነበረው ፤ እንደ ችቦ እየተቀጣጠለ ያበራ ነበር ።

ከላይ በምሳሌ እንደተነገረው የሴትዮዋ ባለቤት ለጨለማ መብራት እንዲሆነው ሚስቱ ያበራችለትን የሻማ መብራት እፍ ብሎ እንዳጠፋው ሁሉ በመጨረሻም በኃጢአት የሰከረው ሄሮድስም ለሱና ለሕብረተሰቡ የጨለማ መብራት የነበረውን መጥምቁ ዮሐንስን አስገደለው ።ለራሱም ለሕዝቡም እንዳያበራ እፍ ብሎ አጠፋው ።

ሄሮድስ ግን ዮሐንስ ከሞተ እውነት ተደብቆ ፤ የሚሰራው መጥፎ ተግባር ሁሉ ሳይገለጥ የሚቀር መስሎት ነበር በተጨማሪም ሕዝቡን እየገዛሁ በሰላም እኖራለሁ የሚል አስተያየት ነበረው ነገር ግን ሌላውን መግዛት ይቅርና እራሱን እንኳን ለመግዛት ባለመቻሉ ሰላም አጥቶ የመንፈስ ደስታ ሳያገኝ እንደሞተ ታሪኩ ይነግረናል ። ይሁን እንጂ መጥምቁ ዮሐንስ ቢሞትም ሥራው አልሞተም ። የትምህርቱም ብርሃን በምዕመናን ሕይወት ላይ ሲያበራ ይኖራል ። እውነትም ተደብቆ አልቀረም የስንዴ ቅንጣት መሬት ላይ ከወደቀች በኋላ እንደገና በቅላ ብዙ ፍሬ እንደምታፈራ ሁሉ የመጥምቁ ዮሐንስም ሞት ብዙ ምዕመናንን ቀስቅሶ የመንፈስ ፍሬ እንዲያፈሩ አደረገ ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ታላቅነትና መልካም ሥራ በሚያስተምርበት ወቅት“ እነሆ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተፃፈለት ይህ ነውና ። እውነት እላችኋለሁ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሳም” ሲል በሕዝብ ፊት ተናግሮለታል የማቴዎስ ወንጌል ም.11 ቁጥር 10-11 ። ይህም ለዮሐንስ ብቻ ሳይሆን እሱን መስለው ለሚሠሩ ሁሉ የሥራ ፍሬ ውጤት ነው ።

እንግዲህ ዮሐንስ መከራ የተቀበለውና የሞተው ለእውነት በአደባባይ ሲመሰክር መሆኑን ተረድተናል ። በዘመናችንስ ስለ ሞራል ውድቀት ስለ ፍርድ ጉድለት ፤ ስለ ጋብቻ መርከስ እንደ ዮሐንስ የሚነድና የሚቃጠል የሚቆረቆር ካህን አለወይ? ይህም ማለት ካህን የሆነ ሰው እንደ እሳት የመንደድ ጠባይ ሊኖረው ይገባል ማለት ነው ። በዚህም የመንደድ ጠባዩ ለቤተ ክርስቲያን መቆርቆር ስለሕዝብ መንደድና መቃጠል በመንፈሳዊ ቅንአት ዝንባሌም ሊኖረው ያስፈልጋል አሁን ያለንበት ዘመን የመሸጋገሪያ ዘመን በመሆኑ ብዙ ችግር አለ ። ትውልድም ከአሮጌው ወደ አዲስ ሁኔታ ለመለወጥ የሚዘጋጅበት ጊዜ ነው ።

ታዲያ በዚህ ጊዜ እንደ ዮሐንስ በመንፈስ የተቃጠሉ በግል ጥቅም የማይደለሉ በግብዝነት የማይለወጡ ፤ ለራሳቸው ሳይሆን ስለሌላው ተላልፈው የሚነዱ ለራሳቸው ክብር ሳይሆን ስለሌላው ክብር መብራት ሆነው የሚያበሩ ፤ ስለ ሌላው ክብር ራሳቸውን የሚያዋርዱ ስለ እውነት በአደባባይ የሚመሰክሩ ካህናት በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ትፈልጋለች ። ያለ መቅረዝ ብርሃን ሊያበራ አይችልምና ።

አለቃ ነቢየልዑል ዮሐንስ



# የተቀደሰ ጋብቻ በደብረ ብርሃን



መምህር ሙሉ ዓለም አየለና መምህርት ሙሉ ዓባይ የጋብቻቸውን ሥነ ሥርዓት በፈጸሙበት ወቅት

በደብረ ብርሃን ሥላሴ ሃይማኖተ አበው ቅርንጫፍ ማህበር አባላት የሆኑት መምህር ሙሉ ዓለም ዓየለና መምህርት ሙሉ ዓባይ በደብረ ብርሃን ከተማ ልዩ ስሙ ጠባሴ በተባለ በደብረ ታቦር መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሚያዝያ 25 ቀን 73 ዓ.ም. በተቀደሰ የተክሊል ሥርዓት ጋብቻቸውን በደማቅ ሁኔታ ፈጽመዋል ።

መምህር ሙሉ ዓለም ዓየለ በደብረ ብርሃን ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ቅርንጫፍ ማህበር ውስጥ ከ1965 ዓ.ም. ጀምሮ በማኅበሩ ውስጥ በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ኃላፊነት ማለትም በዋና ጸሐፊነት፣ በጋዜጠኝነት በመዘምራን ክፍል በኃላፊነት በመምራትና በአዳራሽ አሠሪ ኮሚቴ በአባልነት መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል ። በተለይ ማኅበሩ በቫቲካን ኢምባሲ አማካኝነት በአገኘው እርዳታ የአሠራውን አዳራሽ ከግቡ እንዲደርስና አገልግሎቱ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዲውል ጥረት ተደርጎ ከፍጻሜ ላይ ከአደረሱት መንፈሳውያን ወጣቶች መሐል አንዱ ነው ።

እንዲሁም አጋር የሆነችው መንፈሳዊት እህትም ወ ት ሙሉ ዓባይ በዚሁ ደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ሃይማኖተ አበው ማኅበር ውስጥ በእህቶች ክፍል ፡ በመዘምራን ክፍል ፤ በገንዘብ ያዥነት በእነዚህ የሥራ ድርሻዎች በኃላፊነት በመምራት ከፍተኛ የሥራ አገልግሎትን ከማበርከቷም ሌላ በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን የፍልሰታን ጾሎተ ቅዳሴ ለማስቀደስ ለሚመጡ አረጋውያን፡- ስለ ፍልሰታ ታሪክና አመጣጥ በማስተማር በተጨማሪም ታዳጊ ሕፃናት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሰበሰቡ ማድረግ የዘወትር መንፈሳዊ ሥራዋ ሲሆን በተለይም ማኅበሩ በአሰራው አዳራሽ ላይ የጉልበትና የማስተባበር ኃይል ዋን ስታበረክት የቆየች ወጣት ናት ።

አምላካችንና መድኃኒታችን ክርስቶስ የባረከው ቅዱስ ጋብቻ በቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥነ ሥርዓት በቅዱስ ቁርባን በወጣቶች በኩል ሲፈጸም እጅግ በጣም የሚያስደስትና የሚያስደንቅ ከመሆኑም በላይ ሙሽሮቹ በደብረ ብርሃን ለሚኖሩ ወጣቶች መልካም አርአያና ምሳሌ ሆነዋል ።

ሥርዓተ ቅዳሴው እንዳበቃ በማኅበራቱ መዘምራንና ጥሪ ከተደረገላቸው የመንዲዳ ገዳም መነኮሳዩያት ጋር ያሬዳዊ ዜማዎችን በማሰማት ሙሽራዎችን አጅበው ቤተ ክርስቲያኑን ሶስት ጊዜ ከዞሩ በኋላ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ለፊት እንደቆሙ ከሃይማኖተ አበው ማኅበር ጠ ጽ ቤት ተወክሎ የመጣው ዲያቆን ገዳሙ ደምሳሽ ስለቅዱስ ጋብቻ ምስጢርና ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲሁም ስለመንፈሳዊ ማህበር ዓላማና ጥቅም በሰፊው መልእክት አስተላልፏል። መልእክቱ እንዳበቃ የበዓሉ ፕሮግራም በጸሎት ተፈጽሟል ።

ከተስፋዬ ምንዳ፡-
የደብረ ብርሃን ሥላሴ ሃይማኖተ አበው ቅ ማኅበር ዋና ፀሐፊ



www.ethiopianorthodox.org

# የትግራይ አብያተ ክርስቲያናት

የኢትዮጵያን ታሪክ ለመገምገምና በበለጠ ለማወቅ አብያተ ክርስቲያናት በታሪካዊ ማህደርነታቸው የሚጫወቱት ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው ። አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ረጅም እድሜ ያላቸው መሆኑ ተደጋግሞ ይነገራል ። በአራተኛው ምእት ዓመት ጀምሮ በመስፋፋት ላይ ያለው የክርስትና ሃይማኖት ለአብያተ ክርስቲያናት መስፋፋትና መሠራት ታላቅ ድጋፍ እንዳደረገ ለማንም የተሰወረ አይደለም ። ምንም እንኳ የክርስትና እምነት መስፋፋት በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ቢኖረውም አብያተ ክርስቲያናት በኢትዮጵያ መቼና የት እንደተጀመረ በእርግጥ የታወቀ አይደለም ። ከአካባቢው ሕዝብና ከአፈ ታሪክ እንደተገኘው ከሆነ በስድስተኛው ክፍለ ዘመን ዘጠኙ ቅዱሳን ከመካከለኛው ምስራቅ ከመጡ ጊዜ ጀምሮ የመጀመሪያዎቹ አብያተ ክርስቲያናት እንደተሰሩ ይናገራል ።

በኢትዮጵያ ውስጥ የአብያተ ክርስቲያናት መሠራት መቼ እንደተጀመረ በጽሁፍ የተገኘ ማስረጃ በአስተማማኝ ሁኔታ ባይገኝም ቅሉ ባክስተንና ገርስተር እነዚህ አብያተ ክርስቲናት በዘመነ መሳፍንት ጊዜ ተሰርተው ነበር ይላሉ ። ስለነዚህ አብያተ ክርስቲያናት አሰራር በተጨባጭ ማስረጃ ባይገኝም ቅሉ ከአፈ ታሪክና ከተወላጆቹ አካባቢ የተገኘውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ በትግራይ ክፍለሀገር በገርአልታ አካባቢ ስለሚገኙ ጥንታዊና ታሪካዊ አብያተ ክርስቲያናት በመጠኑም ቢሆን ጨረፍ ጨረፍ በማድረግ እናወሳለን ።

በገርአልታ አካባቢ ስለሚገኙ የታሪክ ቅሪቶችና ጥንታውያን ቤተ መቅደሶች በአካባቢው ያሉት መነኩሴዎችና ተወላጆች እንደሚሉት እነዚህ ቤተ መቅደሶችና ገዳማት ከድንጋይ ተፈልፍለው መሰራት የጀመሩት የኢዛና ዘር በሚባሉት በንጉሥ አብርሃ አፅብሃ በመጀው የኢትዮጵያ ንጉሥ ጊዜ ነው ይላሉ። ሌሎች በገርአልታና በሀውዜን አካባቢ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የተሰሩት በንጉሥ ካሌብ ዘመነ መንግሥት 510 - 588 እና በንጉሥ ገብረ መስቀል (559 - 584 ) ዘመነ መንግሥት ጊዜ ነው ይላሉ ። ሌሎች ከአለት ተፈልፍለው የተሠሩት ቤተ መቅደሶች በአሥረኛው ክፍለ ዘመን በንጉሥ አንበሳ ውድም ዘመነ መንግሥት ( 933 ) ጊዜ ነበር ሲባል በፃዕዳ አምባ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ በንጉሥ ይኩኖ አምላክ (1270 - 1285 ) ዘመነ መንግሥት ተገንብተዋል ፣ እንግዲህ ከዚህ በላይ ስማቸው የተጠቀሰውና ከድንጋይ ከአለት ተፈልፍለው የተሰሩት አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ስማቸው በጊዜው ነግሰውና በሥልጣን ላይ ከነበሩት ንጉሦች ጋር ስለሚመሳሰል በጊዜው በነበሩ ንጉሦች ጥያቄና ትእዛዝ እንደተፈለፈሉና እንደተገነቡ መገመት አያዳግትም ።

አብያተክርስቲያናት በኢትዮጵያ በጌጣጌጥ አሸብርቀውና በተለያዩ ቀለማት አጊጠው መሠራት የጀመሩበት ጊዜ በእርግጥ ባይታወቅም ቅሉ እነዚህ በትግራይ ክፍለ ሀገር የሚገኙ መቅደሶች በግድግዳዎቻቸውና በኮርኒሶታቸው ላይ ያሉት የቅብ ስራዎችና ሥዕሎች ከአስራሦስተኛው እስከ አሥራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ እንደተጌጡ ይነገራል ። በጣራዎቻቸውና ግድግዳዎቻቸው ላይ የተለያዩ ሥዕሎች ጌጦች በመሣላቸው ለቤቱ ተጨማሪ ውበት ሰጥተውታል ። ከዚህም ሌላ ፣ ወንጌልና መንፈሳውያን መጻሕፍት በቅዱሳንና በመላእክት ሥዕል ያጌጡባቸው ቤተ መቅደሶች በብዛት በዚችው ክፍለ ሀገር ይገኛሉ ። ምንም እንኳ ለሥዕሉ መስሪያ የተጠቀሙባቸውን የቅብ መሳሪያዎችም ሆነ የስዕሉ ሥራ በምን ዓይነት እንደተካሄደ በዝርዝር የታወቀ ባይሆንም በየቤቱ ማእዘናት የተለያዩ ሥዕሎች ተስለው ይገኛሉ። በጊዜው የነበሩ የሥዕል ስራዎች ከቢዛንታይን ሥዕል ጋር አንድ እንደሆኑና የቢዛንታይን የሥዕል ስልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ ጠልቆ በመግባት የተስፋፋ መሆኑ ተደጋግሞ ይነገራል፣ ይሁን እንጂ ሥልጣኔውም ሆነ ጥበቡ ኢትዮጵያዊ የአሠራር ስልት እንደሆነ ታውቋል ።

በትግራይ ክፍለ ሀገር የሚገኙትን ጥንታውያንና የብዙ ምዕት ዓመት እድሜ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ አመጣጥና አሰራር ለማወቅ በእርግጥ ብዙ ጥናትና ምርምር የሚያስፈልገው ነው ። የአብያተ ክርስቲያናተ አሰራርና ቅርጽ ብዙም አልተጠናም ። አቀማመጡ ግን በተራራ ጫፍ ላይ የተመሰረተና በኮረብታ የተከበበ ነው ። የቤቱ አሰራር በስሊካ የሚባለውን የቤት አሰራር ዘዴ የተከተለ ነው ። ይህ ቤት ከመሀሉና ከጎኑ ረዘም ብሎ መካከሉ ክብ ነው ። የዚህ አይነት የቤት አሰራር በሕዝቡ ዘንድ የበለጠ ሲታወቅ ለሕዝቡ አዲስ የቤት አሰራር ዘዴ ሆኖ ለዘመናት ቆይቷል ። በትግራይ ክፍለሀገር የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት አሰራር ዘዴ ከጥንታውያን አክሱማውያን ግብረ ህንፃ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው ይባላል ። የተሠሩትም አብያተ ክርስቲያናት በመንፈሳዊ ሥዕሎች እንዲጌጡና እንዲያምሩ ሁነው ተሰርተዋል ። የቤተ መቅደሶቹም ባለሙያዎች በሥዕል ለማሳመር የሥነ -ን ጥበብ ከግብፅና ከግሪክ እንደተማሩት ይነገራል ፣ ምክንያቱም ግብፆች በሥዕል ሥራ በጊዜው የሰለጠኑ ከመሆኑም በላይ በጊዜው ታዋቂነትና በዓለም ላይ የቆየ ታሪክ ያለው ቤተመቅደስ በዚያ ነበርና ነው ።

በትግራይ ክፍለ ሀገር የሚገኙ ጥንታውያንና ታሪካዊ የሆኑት ቤተመቅደሶችና ገዳማት በድንጋይና ከአለት ተፈልፍለው ምቹ ቦታ ላይ ሳይሆኑ ከተራራ ጥግና ጫፍ በብዙ ልፋትና ከባድ ጥረት ለታሪክ ያለፉ የጥንታዊ ሰው የልፋቱ ውጤት ናቸው ። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ ነገሥታት የተሰሩ ናቸው። ከነዚህም አብዛኞቹ ገርአልታ በሚባል አካባቢ ይገኛሉ ።

በገርአልታ አካባቢ ከሚገኙት አንዱና ትልቁ ቤተክርስቲያን አብርሃ ወአፅብሃ የተባለው ቤተክርስቲያን ነው የአብርሃ ወአፅብሃ ቤተ ክርስቲያን ከነጭ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሰራና ደብዘዝ ያለ ያረጀ ቅርፅ ያለው ቤተክርስቲያን ነው ። ይህ ቤተ ክርስቲያን በጣም ሰፊ ከመሆኑ በላይ እጅግ በ ·ዋቡ መንፈሳዊ ሥዕሎች የተንቆጠቆጠ ነው ሥዕሎቹ የተሣሉት ግድግዳዎቹ ላይ ብቻ ሳይሆን ጣራውም ቢሆን ያሸበረቀ ስለሆነ እዩኝታው ግሩም ድንቅ ነው ። በግዝፈትም ቢሆን በትግራይ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የሚወዳደረው የለም ። ብዙ ላብና ወዝ ፈሶበት የተሰራው ይኸው ቤተክርስቲያን በውበቱ የደስደስ ያለው ቤተመቅደስ ነው ።

ከአብርሃ አጽብሃ ቤተክርስቲያን ትንሽ ራቅ ብሎ በኮረብታማ ቦታ ላይ የተሰራውና ሌላው ባለታሪክ ቤተክርስቲያን ደግሞ ሚካኤል መንጻዓ ነው። ሚካኤል መንጻዓ አነስተኛ ቤተክርስቲያን ከመሆኑም በላይ እንደአብርሃ አጽብሃ ቤተክርስቲያን ጌጣጌጥና ሥዕሎች የለውም ከዚህም ሌላ ይህ ቤተ መቅደስ በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ነው ።

ወደ ሌላው ቤተክርስቲያን ስናመራ ደግሞ ደብረጽዮን የተባለውን ጥንታዊ ቤተመቅደስ እናገኛለን ። ደብረጽዮን በጣም ሰፊና ከነጭ አለት ተወቅሮና ተቦርቡሮ የተገነባ ቤተ ክርስቲያን ነው ። ደብረጽዮን በተለያዩ መንፈሳዊ ሥዕሎች ግድግዳዎቹ ያሸበረቁ ሲሆን የሥዕሉ ቅብ ከአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን በፊት የነበረ ሥልጣኔ ያፈራው ጥበብ እንደነበር ይገመታል ።

ሌላው ማራኪና ብዙ ዘመን በመቆየት የጊዜን ጥርስ ተቋቁሞ በዘመናችን የምናየው ቤተክርስቲያን ደግሞ ዮሐንስ መቅዳ የተባለ ጥንታዊና ታሪካዊ ቤተክርስቲያን ነው ። ይህ ቤተ መቅደስ ከአንድ ወጥ አለት ተፈልፍሎ የተሠራ ሲሆን ዝቅተኛ ደረጃ ባለው የማለል ሥራ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ታሪክና የዘጠኙ የሲሪያ ቅዱሳን ምስል ይገኙበታል ። እነዚህ ቅዱሳን ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ከሲሪያ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ቋንቋየተረጎሙ ናቸው ተብሎ ይገመታል ። በደቡብ በኩል በሚገኘው የቤተመቅደሱ ክፍል ገጽ ደግሞ ንጉሥ ፋሲል 1632 - 1667 በፈረስ ላይ ተቀምጠውና አሽከር ከኋላቸው አስከትለው የሚያሳይ ሥዕል ተሥሎበታል ።

የዚህ ቤተ ክርስቲያን

አካባቢ የሚገኙ አብያተክርስቲያናት ታሪክ ከአራተኛው እስከ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ሲታሰብ ፣ የቤተ መቅደሶቹ ቅብና ጌጣጌጥ ሥራ ግን ከአስራዕስተኛው እስከ አስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ የተሰሩ መሆናቸው ይነገራል ። በትግራይ ክፍለ ሀገር በገርአልታ አካባቢ የሚገኝ ጥንታዊና አንጋፋው ቤተ ክርስቲያን የደብረ መዓር ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ነው ደብረ መዓር ጊዮርጊስ 500ሜትር ከፍታ ላይ የተሠራ ሲሆን፣የ ቤተ መቅደሱ አንድ ሦስተኛው ክፍል ከ እንጨት ቀሪው ክፍል ደግሞ ከአለት ተፈልፍሎ የተሠራ ቤተ መቅደስ ነው ፣ ቤተመቅደሱ በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ሥዕሎች ያማረና ያጌጠ ከመሆኑም በላይ ከአለት የተሰራው የቤተክርስቲያን ሥዕል ከአክሱማውያን የሥዕል ስራ ጋር ይመሳሰላል ። ወደ ደቡብ ዱጋም ስናመራ ሌላው የምናገኘው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ዱጋም ማርያም አሮፋዳ ነው፣ይህ ቤተ ክርስቲያን መላውን ከአለት ተፈልፍሎ የተሰራ ነው ። ስፋትና ርዝመትም ያለው ሰፊ ቤተ ክርስቲያን በመሆኑ እንደሌሎቹ መቅደሶች በተለያዩ ሥዕሎችና ጌጣጌጦች ያጌጠ አይደለም ።

ማርያም ጳጳሲት ሌላው የብዙ ዘመን እድሜና ታሪክ ያሳለፈ ቤተክርስቲያን ነው ። ማርያም ጳጳሲት ከአለት ተፈልፍሎ የተገነባ ሲሆን ለታቦቱ መቀመጫ የተለየ ክፍል ያለው ነው ። በዚህ ቤተ መቅደስ ላይ የተሰሩት መንፈሳዊ ሥዕሎች የአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ከመሆኑም በላይ ብዙ ምእት ዓመታት ያሳለፈ ጥንታዊ ቤተክርስቲያን ነው ።

ከማርያም ጳጳሲት ትንሽ ተጉዞ ሚካኤል አረጋዊ የሚባል ሌላ ቤተክርስቲያን ይገኛል ። የቤተ ክርስቲያኑ ስም የተወሰደው ከዘጠኙ የሲሪያ ቅዱሳን የአንዱ ሲሆን ከአለት ተፈልፍሎ የተሰራው ክፍል የሠላሳ ሜትር ከፍታ ሲኖረው ፣ አንዱ ቅዱስ ወደ ቤተመቅደስ ሲጓዝ የሚያሳይ ሥዕልና ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ሲያጥብ የሚያሳይ ሥዕል አለው ።

ሌላው ሰፊና ትልቅ ቤተክርስቲያን ደግሞ ማርያም ቆርቆር የሚባለው ነው፣ ማርያም ቆርቆር ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ሥዕሎችና ጌጦች በየግንቦቹና በየማእዘናቱ ላይ ተሥለው ይታያሉ ። በእያንዳንዱ ግድግዳ ላይ የአስራ አምስተኛውን ክፍለ ዘመን የሥዕል ሥራ የሚያንፀባርቁ የሥዕል ንድፎች ይገኛሉ ። ይሁን እንጂ እነዚህ ሥዕሎች በተለያዩ ሁኔታዎች ከፊሎቹ ደብዝዘው ከፊሎቹ ደግሞ ጥንታዊ መልካቸውና ውበታቸው ጠፍቶ ኪነታዊ ጸጋቸው ተገፎ ይታያል።

ከማርያም ቆርቆር ትንሽ ተጉዞ የአባ ዳንኤል የጸሎት ቤት ይገኛል ፣ ሁለት ክፍል ያለው ይኸው የጸሎት ቤት በቀለም የተቀባ ሲሆን ግድግዳዎች በቢዛንታይን የስእል ሥራ የተንቆጠቆጡ ናቸው።አባ ይምዓታ የሚባለው ቤተክርስቲያን በጥሩ የግድግዳ ጌጦች ያጌጠና ትግራይ ውስጥ ከሚገኙት አብያተክርስቲያናት ደስ ከሚሉት አንዱ ነው።የቅዱሳንና፣የመላእክት የብሉይ የሐዲስ ኪዳንና በጠቅላላውም መንፈሳዊያን ሥዕሎች ጎልተው ይታዩበታል ። ከዚህም ሌላ ደብዘዝ ብለው የሚታዩት በግራና በቀኝ በኩል የተሣሉት ሥዕሎች በጣም ደስ የሚያሰኙ ሲሆኑ አባ ይምዓታ በበቅሎ ላይ ሆነው የሚያሳይ ሥዕል የደቀ መዛሙርቱ ሥዕል በጉልህ መንገድ ተሥሎ ይታያል ።

በገርአልታ አካባቢ ከሚገኙት ቤተ መቅደሶች አንዱ ደግሞ አርባእተ እንስሳ የተባለ ቤተ መቅደስ ነው ። መካከለኛ እርዝመት ያለው ይህ ቤተ ክርስቲያን ድጋፍ ሰጪ የሆኑ ብዙ ምሰሶዎች አሉት። ከዚህም በቀር ውብ የሆኑ መንፈሳዊያን ሥዕሎች በግድግዳውላይ ሲታዩ የአራቱ

ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

## ክርስቲያናዊ ጋብቻ

«እግዚአብሔር አምላክ በአዳም ከባድ እንቅልፍ ጣለበት አንቀላፋም ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ሥፍራውን በሥጋ ዘጋው እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሰራት ወደ አዳምም አመጣት ። አዳምም አለ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርሷ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል ፤ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል አንድ ሥጋ ይሆናሉ ኦሪት ዘፍ 2 ቁ 21 - 24 ።

ከዚህም ሌላ ረዳት እንድትሆነው ሔዋንን ለአዳም የሰጠው አምላክ ጋብቻ ከሁሉ ይልቅ የከበረና የሕይወት አንደኛው ክፍል መሆኑን ለማሳወቅ የመጀመሪያ ተአምሩን በሠርግ ቤት ፈጸመ ። ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለምና ለአዳም ረዳት እንፍጠርለት ያለውን ቃሉን በማስታወስም ጋብቻን በመጀመሪያ ቀደሰ ። ከዚያ በኋላ ሌሎቹን የሕዝብ አገልግሎቶቹንና ድንቅ ሥራዎቹን ማከናወኑን ቀጠለ ፤ የሚለውን ቃል በቅዱስ መጽሐፍ ስንመለከት ጋብቻን ከሁሉ በፊት አድርጎ እንዴት እንዳከበረውና እንደቀደሰው እንረዳለን። ከሌሎቹ ድንቅ ድንቅ ሥራዎቹ በፊት ጋብቻን ያከበረበት ምክንያት በብዙ መንገድ ሲተነትን ከነዚህ ውስጥ በቂ መልስ ሊሰጠን የሚችለው

- ሰዎች ከሁሉ በፊት ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባና አስፈላጊ መሆኑን ለመጥቀስ

« አዳም ሔዋንን » ስጠኝ ብሎ ሳይጠይቀው እንደሚያስፈልገው አይቶ ስለሰጠው በዚያም ያለውን ጉድለት እርሱ ማሟላት እንዳለበትም ስለሚያውቅ በሠርጉ ቤት ያለቀባቸውን የወይን ጠጅ ጭምር ሳይጠየቅ ... 

ሰጠው በዚያም ያለውን ጉድለት እርሱ ማሟላት እንዳለበትም ስለሚያውቅ በሠርጉ ቤት ያለቀባቸውን የወይን ጠጅ ጭንቀታቸውንና ጉድለታቸውን በእመቤታችን በኩል ተረድቶ ካዘጋጁት የበለጠ አድርጎ በሠራላቸውው ጊዜ ለጋብቻ ከሁሉ በፊት ታላቅነትን በመስጠት ለሚኖረው ጉድለት (እክል ) ሁሉ ረዳት መሆኑን



ጋብቻቸውን በተክሊልና በሥጋ ወደሙ የፈጸሙ ዲያቆን አሰፋና ወ ት የማታ ወርቅ

መግለጹ እንደሆነ አይጠረጠርም ።

ስለዚህም ይመስላል አባቶች « ሚስት ስትፈልግ የአዳምን እንቅልፍ ተኛ »ሲሉ የሚናገሩት ለሴቷም እንደዚህ ነው ። ከፍ ብሎ ከራሱ ዝቅ ብሎ ከእግሩ ሥር ሳይሆን ሌላም አጥንትን መፍጠር ሳይሳነው የሁለቱን እኩልነት ለመግለጽ ከአዳም አንዲት የጎኑን አጥንት በማውጣት ሔዋንን አስገኝለት ።

አዳምም ይኸንን ባማወቅ አጥንቷ ከአጥንቴ ሥጋዋም ከሥጋዬ ነው ስለዚህ ሕይወቴ ናት በማለት የመጀመሪያዎቹ ሰዎችና የጋብቻም መሠረት አዳምና ሔዋን መሆናቸው በዓለም የታወቀ ነው ።

ከዚህም ሌላ ክርስቶስ ሠርግን በእርሱና በቤተክርስቲያን መካከል ላለው ግንኙነት ምሳሌ በማድረግ አቅርቦታል። እርሱ ሙሽራው ሲሆን ሙሽራይቱ ቤተ ክርስቲያን ናት ። በዚህ ሁኔታ ወንድና ሴት በተቀደሰ ጋብቻ እንዲዋሃዱና ቤተሰብ እንዲያቋቋሙ ይፈለጋል ።

ይኸውም ለሰብአዊ ዘር ሁሉ የበረከት ምንጭ ሆኖ እስከ ዛሬ ድረስ በዓለም ላይ የሚያልፉትንና የሚመጡትን ትውልዶች ሲያስገኝ ኖሯል ወደፊትም ይቀጥላል ። ለዚህ ሁኔታ ሁሉ ሃላፊነት የተጣለበት ጋብቻ በረከት የመላበት ቤተሰብ ሊያስገኝ የሚችለው ታዲያ በተቀደሰ ሥርዓት የተፈጸመ እንደሆነ ነው በዚያም ውውስጥ ፍቅር ሰላም ትእግሥት ርኅራኄ በጎ ነገሮች ሁሉ ይገኛሉና ። ከዚያ ውጪ በሚፈጸመው ጋብቻ ግን ለሰው ዘር ሁሉ መርገም የሚሆኑ ነገሮች ይከቡታል ቆጥረን አንጨርሰውም ና እን

ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል



# ይህን ያውቁ ኖሯል ?

እጅጉ ረታ

ካለፈው የቀጠለ

በተነገረው ትንቢት መሠረት ኢየሩሳሌም ልትጠፋ ገና 4 ዓመት ሲቀራት ----66 ዓ.ም ላይ ማለት ነው --- የዳስን በዓል ለማ ነበር ወደ ኢየሩሳሌም ከመጡት አይሁድ መካከል አንድ ሰው ነበር ። ኢያሱ ወልደ አናንያስ የሚባል። ያልተማረ ጨዋ ፤ እንዲያው ምንም ምን የፊደል ዘር ያልቆጠረ። በዓሉን ለማክበር በቤተ መቅደሱ ግቢ እንዳለ ሳይታሰብ ድንገት አፈፍ ብሎ ተነስቶ ፤ ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰምቶ « ቃል ከምሥራቅ ቃል ከምዕራብ ! ቃል ከአራቱም ማዕዘን ! » የሚለውን ራሱ እንኳ የሚያስተውለው አይመስልም ---- ብቻ መናገር ጀመረ ።» ኢየሩሳሌም ሆይ ወዮልሽ ! ወዮታ አለብሽ ! ቅጽርሽ ይፈርሳል ! ቤተ መቅደስሽ ይተኮሳል!!ይብላኝለት ለሙሽራው ! ይብላኝላት ለሙሽራይቱ! ለልጆችሽ ይብላኝላቸው ! .........ወዮ ወዮ ..... » ከዚያን ዕለት ጀምሮ በየደረሰበት ቦታ ሁሉ ሳንቃው እስኪደርቅ ሌት - ተቀን እየ ጮኸ ይለፍ ይናገር የነበረው ዋይታ ብቻ ነበር።ገዓር ስቆቃው ኢየሩሳሌም ሆይ ወዮልሽ ወዮታ አለብሽ።እንግዲህ ይህ ሁሉ ገና አገር አማን በነበረበት፡ ጦርነትና የጦርነት ወሬ ባልተሰማበት ፤ ሀገሪቱ ፍጹም በሆነ ሰላምና ፀጥታ ላይ ትገኝ በነበረበት ወቅት ነበር። ታዲያ በተደጋጋሚ ሳያቋርጥ የሚናገረው ይህ ለጆሮ የሚቀፍ ከባድ ነገር ያታከታቸው ሰዎች በዘንግ ቢደበድቡት ቢወግሩት ይህን ዋይታ ይህን ስቆቃው ሊያስጥሉት አልቻሉም ። ሲሄድ ሲመለስ፣ ሲቀመጥ ሲነሳ እንደበተ የሚጥለው ወዮታ ብቻ ! ገዐር ፣ ስቆቃው « ወዮ ለዚች አገር ። »ከዛሬ ነገ ይተዋል ብለው ቢያዩት ፣ ቢጠብቁት የማይተው መሆኑን የተረዱት የአይሁድ ካህናትና የሕዝቡ አለቆች ነገሩ በጣም ስላስቆጣቸው ከሮማዊ ገዥ አቸው ከአልቢኑስ ፊት አቀረቡት ። ሹሙም ይህን መዓት - አውሪ ሰው ማንነቱን ፣ ከየት የመጣ መሆኑን፡ ፣ እንዲህ ያለውንስ የሚያሸብር ነገር ከየት አግኝቶ የሰው ጆሮ እንደሚያደነቁር እንዲነግረው ቢጠይቀው መልስ ሊሰጠው አልቻለም አልፈለገም የሚሰጠው መልስ ሁሉ ያው የተለመደ ወዮታ ብቻ ነበር«ኢየሩሳሌም ሆይ ወዮልሽ ወዮታ አለብሽ...»የሞኝ ዘፈን ሁልጊዜ አበባዬ እንደሚባለው የሀገራችን ምሳሌ ። ከዚያም ጥለው አጋድመው ሥጋው አልቆ አጥንቱ እስኪታይ ድረስ ጀርባውን ሲተለትሉት እንዲተውት አለመነም ። አጥፍቻለሁ ተሳስቻለሁ ብሎ ይቅርታ ምሕረት አልጠየቀም። ቅንጣት ያህል ጠብታ እንባ አልወረደውም። ብቻ እያንዳንዱ የጅራፍ በትር ሲያርፍበት « ኢየሩሳሌም ሆይ ወዮልሽ ወዮታ አለብሽ ...»እህ ! እያለ በማቃሰት የሚሰጠው መልስ ። በመጨረሻም ሁኔታው ገዥውን ግራ ስላጋባው « ምን ዓይነት ሰው ነው ? » ብሎ እንዲለቀው አድርጓል ።

ይህ ሰው ከዚያን ጊዜ በፊት የጀመረ ሌት - ተቀን ያለማቋረጥ ፣ ያለማሰለስ ጉሮሮው እስኪዘጋ ድረስ በመጮህ በከተማይቱ ፣ በቤተ - መቅደሱ ፡ በሕዝቡ ላይ እንዲሁ ወዮ ! ወዮ ! ..... እንዳለ፣ በየአደባባዩ ፣ በየገበያው ፣ በየምኩራቡ በየመንገዱ እንዲሁ እንደጮኸ ፤ ወዮውን ፣ አላፊ አግዳሚውን እንዲሁ እንዳሰለቸ ፣ ፀጥታው ሰላሙ ደፍርሶ በድንገት ጦርነቱ ለመፈንዳት በቃ።ንገሩ ደርሶ የጦርነቱ እሳት ሲቀጣጠል ዐይኑ ካየ በኋላ ብቻ ለጥቂት ጊዜ ድምጹ ጠፍቶ እርጭ ብሎ ነበር ። በኋላ ግን ጦርነቱ እየጋመ እየተፋፋመ ሲሄድ « እንደገና ወዮ ! ወዮ ለዚች ከተማ ! ለቤተ መቅደሱ ወዮ! ወዮ! ለዚሁ ሕዝብ «ዋይታ ስቆቃው የራሄል እንባ ዓይነት ። በመጨረሻም« ወዮ ለራሴ ወዮልኝ ወዮታ አለብኝ ......» ገና ጨርሶ ከአፉ ሳያወጣት ፣ ከሮማውያን በኩል ከተደቀነ መሳሪያ የተተኮሰ ( የተወረወረ) ደንጊያ ልብ ራሱን ብሎት ትንፋሹ ወዲያውኑ ቀጥ ! ብሎ ! በዚሁ አበቃለት ። ስለከተማይቱ፣ ስለቤተ መቅደሱ፣ እንዲሁም ለራሱ የተናገረው ነገር እነሆ ደረሰ ተፈጸመ አንድም አልቀረ። የእርሱ ዋይታ፣ የእርሱ ገዐር የማስጠንቀቂያ ደወል ነበር ። ወደ ንስሐ ፣ ወደ ፀፀት የሚመራ ፣ ግን ሰሚም አድራጊም አላገኘም የእኛ የሰው ልጆች ባሕርይ ምን - ጊዜም ጠማማ አይደል!እውነትን መስማት ማየት የማይወድ ?



## የትግራይ አብያተ ....

ከገጽ ፲፱ የዞረ

ወንጌላውያን ሥዕል ሌላው የቤተ ክርስቲያኑ ውበት ነው አሁንም በገርአልታ የጴጥሮስ ቤተ መቅደስ አለ ። ይህ ቤተ መቅደስ በሁለት የቤት አሠራር ሁኔታ የተከፈለ ሲሆን አንደኛው የቤተ መቅደሱ አሠራር ከዝግባ ፤ ሌላው ደግሞ ለታቦቱ መቀመጫ ተብሎ የተሰራ ክፍል ከአለት የተሰራ ነው ፤ ቤተ ክርስቲያኑ ምንም እንኳን ትልቅ ባይሆንም ቅሉ ባለው የቤት አሰራርና የቅብ ሥራ ደስየሚያሰኝ ነው ከአለት ተፈልፍሎ የተሰራው የዚህ ቤተ ክርስቲያን ክፍል የክርስቶስን ሥዕል ሲያሳይ ከእንጨት የተሰራው ክፍል ደግሞ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ሥዕሎችን ያሳያል ።

ሚካኤል ሌላው በገርአልታ አካባቢ የሚገኝ አንጋፋ ጥንታዊ ቤተክርስቲያን ነው ይህ ቤተ ክርስቲያን ጣራው ክብ ሆኖ ከድንጋይ የተቀረጸ ነው ።

መድኃኔ ዓለም ደግሞ ትልቅና ማራኪ የሆነ ቤተክርስቲያን ነው ። ይህ ቤተ ክርስቲያን ትግራይ ውስጥ ከሚገኙት ብዙ ዘመናት ካሳለፉት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ነው ።

ቂርቆስ ወርቁ የተባለው ማራኪ ቤተ ክርስቲያን በጣም ትልቅ ቤተመቅደስና ውብ የአሰራር ስልት ያለው ቤተ ክርስቲ

www.ethiopianorthodox.org

ያን ነው ። በተጨማሪም ይህንን ቤተክርስቲያን ለመስራት ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል የተሰማራበትና ብዙ ገንዘብ እንደ ፈሰሰበት ከሚታየው የቤተ መቅደሱ አሰራር ለመገመት አያደግትም ። አፈታሪኩ እንደሚያመለክተው ከሆነ ይህ ቤተመቅደስ የተገነባው ከሦስት መቶ እስከ ሦስት መቶ አምሳ ስድስት ዓ.ም ነው እየተባለ ይነገራል ።

በትግራይ ክፍለ ሀገር ብዙ የሚደነቁና የብዙ ምዕት ዓመት እድሜ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በእርግጥ ይገኛሉ። ከዚህ በላይ የቀረቡት ከሞላ ጎደል ከክፍለ ሀገሩ የሚገኙት ጥናት የተደረገባቸው አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ።

ያለፉትን ብዙ ሽህ ዓመታት ወደ ኋላ ተመልሰን ስናስብ በአገራችን ግሩም ድንቅ የተሰኙ እነዚህን የመሳሰሉ አብያተ ክርስቲያናት ይታሰቡናል እነዚህ ፣ ከረጅም ዓመታትና ከብዙ ትውልድ በፊት የተሠሩት ቤተ መቅደሶች የጥንታዊት ኢትዮጵያ ሰው በዘመኑ ባለውና ባገኘው የሥልጣኔ ልምድ አውቦ ፣ አጊጦና አሸብርቆ ለተተኪው ትውልድ ያስተላለፋቸው የታሪክ ቅርሶቻችን ናቸው ፣ እንደዛሬ የሰለጠነ የሰው ኃይል መሀንዲስ ባልነበረበት በዚያ ዘመን ከታላላቅ ተራራዎች አካባቢ ከድንጋይ ፈልፍሎ የዓለም ሕዝብ እንደ ትንግርት የሚያያቸውን እነዚህን ቤተ መቅደሶች መስራቱ በጥበቡ ምን ያህል የተካነ እንደነበረ ያመለክታል ።

እነዚህ የሀገሪቱ ቅርሶች የብዙ ዘመን እድሜ ያሳለፉ ከመሆናቸውም በላይ በዓለም ላይ ከሚገኙት ጥቂት አስገራሚዎች ከፍተኛ ተደናቂ ነገሮች እንደ አንዱ በመሆናቸው የዓለም ሕዝብ በአድናቆት ይመለከታቸዋል ።

በባህልና እስፖርት ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና የባህል ዜና አገልግሎት ክፍል ከሚያዘጋጀው « ዜና ባህል » መጽሔት ቅጽ 3 ቁጥር 7 መጋቢት 30 ቀን 1973 ዓ.ም. ከአወጣው እትም የተገኘ፣

---

## ክርስቲያናዊ ጋብቻ

ከገጽ ፭ የዞረ

ተወው ። ሁለቱ ባለትዳሮች ራሳቸውን ብቻ ለማስደሰት የሚተጉበት ስለሚሆን ሥረ መሠረቱ የተዛባ ይሆናል ። «ራሱን ብቻ ለማስደሰት የሚፈልገ ሰው ትዳርን ባይመሠርት ይሻላል» ሲል አንድ ሊቅ ደምድሞታል ። ጋብቻ ሁለቱን ሕይወታቸውን አንድ ለማድረግ የሚያስገቡበት ክብ ነገር ነው ማለት ይቻላል።

ከጋብቻ በኋላ አንዳችም ቢሆን የሚለያዩበት የለምና ከጋብቻውቸው ዕለት ጀምረው « ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ይህ ታላቅ ምሥጢር ነው » ሲል ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን 5 ቁ 31 ላይ በተናገረው መሠረት አቶ አሰፋ ሀ/ ሚካኤልና ወ/ ት የማታ ወርቅ ለውጤ በመንበረ መንግሥት ቅ/ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በሥርዓተ ተክሊልና ቅዱስ ቁርባን ጋብቻቸውን ፈጽመዋል ።

ከሥርዓተ ቅዳሴውም በኋላ በቅጽረ ቤተክርስቲያኑ ለበዓሉ የተጠሩት ዕድምተኞች የሻይና ቁርስ ግብዣ ተደርጎላቸው ሲካሄድ የቆየው ሥርዓት አብቅቷል።

ስለሙሽራውና ሙሽራይቱ የሕይወት አካሄድ ከብዙው በጥቂቱ መጥቀስ ቢያስፈልግ አቶ አሰፋ ሀ / ሚካኤል የቤተ ክርስቲያንን ትምህትና ዘመናዊውንም የሙያን የቀለም ትምህርት በሚገባ ተከታትለው ያጠናቀቁ በመሆናቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እጅግ የታረቁና የተስተካከለ አካሄድ ያላቸው ሲሆኑ የሙሽሪቷም የወ/ ት የማታ ወርቅ ለውጤ ያላት መንፈሳዊ አካሄድ ከእርሳቸው ተለይቶ የማይታይ ነው ።

ስለዚህ ነው ሁለቱ ወጣቶች ባላቸው መንፈሳዊ ሕይወት ተመራርጠው በተቀደሰ ጋብቻ ውስጥ እራሳቸውን ያስገቡት በዚህ ሁኔታ አዲስ የመሠረቱት ጋብቻ ፍሬው መልካም ሊሆን እንደሚችል የታመነ ነው ። አንድ ዓይነት ሕይወት ባላቸው ሙሽሮች ትክክለኛው ሥርዓትና በሕይወታቸው ሊያደርጉት የሚገባቸውን አንደኛውን ፈጽመዋልና ነው።

እኛም ሙሽሮቹ የመሠረቱት አዲሱ ኑሮ የተቃናና የተስተካከለ እንዲሆንላቸው እየተመኘን ለእነርሱና ለአንባቢዎች የምናስተላልፈው ምክር አዘል መልዕክት ቢኖር

- እርስ በርሳችሁ እየተዋደዳችሁ ኑሩ
- እግዚአብሔርን የቤታችሁ ጠባቂና መሪ አድርጉት
- እርስበርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ

-ያለውን ጉድለት ለመመልከት ጊዜም አትስጡት መልካሙን አካሄዳችሁን ተከታተሉ ከዚህ በተረፈ ግን ይኸን መልካም አርአያነት ሌሎች ወጣቶች ሁሉ ሊመርጡትና ሊከተሉት በጋብቻ በኩል ያላቸውን የሕይወት አካሔድ ሊወስኑበት እንደሚገባቸው በዚህ አጋጣሚ ጊዜ እንጠቁማለን ።

## ዜና ሊቃውንት

ከገጽ ፯ የዞረ

ንፈሳዊ አስተዳደር ችሎታቸው ስልት ብቻ ሳይሆን በተለይ በቅኔ ምርምርና ይዘት ያበረከቱት ከፍተኛ የሆነ የሞያ መግለጫ አስተዋጽኦ ነበር ።

መምህር በትምህርት ጉባኤያቸው ለ ደቀ መዛሙርቶቻቸው መንገድ ልዩ ልዩ የሆነ ቅኔ ዘርፈዋል በአድባራትና በገዳማትም በታወቁ ታላላቅ በዓላት ሰሚዎችንና ምሥጢረ ቅኔ ተከታታዮችን የሚስቡና መታሰቢያዎች የሚሆኑ ቅኔዎችን ተቀኝተዋል ።

ለማስረጃም ያህል ስለሩፋኤል በዓል የተቀኙት መውድስ ቅኔ እነሆ ከዚህ ቀጥሎ በግዕዝና በአማርኛ ተገልጿል።

ተከታዩ ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



## ልማት በቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን የልዩ ልዩ ልማቶች መፍለቂያና የመንፈሳዊም ሆነ የሥጋዊ ጥበብ ምንጭ ሁና መቆየቷ ቢታወቅም ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን ኋላቀር በመሆን የልማት ሥራዋን ወደ መዘንጋት ተቃርባ እንደቆየች ግልጽ ነው ።

ባሁኑ ጊዜ ግን ለቤተ ክርስቲያንና ለአገልጋዮቿ ካህናትና ዲያቆናት እመቸለ ምእመናንም ቀና መንገድ መሰጠት የልማትንም ሥራ ማስፋፋት አስፈላጊ መሆኑን በማመን በሰበካ ጉባኤ ትጋትና ጥረት የልማት እንቅስቃሴ በመካሄድ ላይ ነው ለዚሁም በሸዋ ሀገረ ስብከት በመራ ቤቴ አውራጃ በሚዳ የሚገኙ 18 የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት የልማት ሥራ በማከናወን ላይ መሆናቸውንና ይህንንም የልማት ሥራ እንዴት እንደጀመሩትና በምን ዓይነት እንደሚንቀሳቀሱ የአራጃው ቤተክህነት ሥራ አስኪያጅ አቶ ጌታቸው ኃይሌን አነጋግረናቸዋል።

ትንሣኤ በመራቤቴ አውራጃና በሚዳ ወረዳ ካህናቱና ምእመናኑ በሕብረትና ባንድነት የልማት እንቅስቃሴ መጀመራቸውን ከሸዋ ሀ/ ስብከት በተለላፈልን ሪፖርት ለማረጋገጥ ችለናል ። በዚህም አጋጣሚ ሥራው እንዴት እንደ ተጀመረ በይበልጥ ስለሚያውቁት ሁኔታውና ስለ ልማቱ እንቅስቃሴ ቢያብራሩልን

አቶ ጌታቸው ኃይሌ በዚህ በሚዳ ወረዳ 37 አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ከእነዚህም ከ37 አብያተ ክርስቲያናት መካከል ባሁኑ ጊዜ በልማት ሥራ ተባብረው የሚገኙ 18 አብያተ ክርስቲያናት ናቸው እነዚህም ተባብረው የእርሻን ልማት ያቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናት ስም ዝርዝርና የሠራተኞቹ ብዛት የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ በመራኛ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ 28 ጥማድና 15 ዶመኛ
2ኛ የደብረ ገሊላ ቅድስት ማርያም 78 ጥማድና 15 ዶመኛ
3ኛ የአባቢሎ ማርያም 23 ጥማድና 20 ዶመኛ
4ኛ የአገማ ኢየሱስ 25 ጥማድና 15 ዶመኛ
5ኛ የአሸረር ሥላሴ 15 ጥማድና 9 ዶመኛ
6ኛ የሚዳ ቅዱስ ሚካኤል 40 ጥማድና 30 ዶመኛ
7ኛ የአጣኔ መስፈርያ መግደላዊት ማርያም 30 ጥማድና 10 ዶመኛ
8ኛ የሞዴል ቅዱስ ጊዮርጊስ 22 ጥማድና 13 ዶመኛ
9ኛ የደብረ ጊድ ሥላሴ 10 ጥማድና 10 ዶመኛ
10ኛ የሶርት አቡነ መልከጼዴቅ 35 ጥማድና የአትክልት መሬት ተረክበናል
11ኛ የሞዓት ቅዱስ ጊዮርጊስ 15 ጥማድና 22 ዶመኛ
12የገደላ ቅዱስ ጊዮርጊስ 27 ጥማድና 7 ዶመኛ .
13ኛ የአካ . ቅዱስ ገብርኤል 12 ጥማድና 5 ዶመኛ



አቶ ጌታቸው ኃይሌ

14ኛ የሚል ማርያም 13 ጥማድና 18 ዶመኛ
15ኛ የክርክሬ ቅዱስ ጊዮርጊስ 29 ጥማድና 9 ዶመኛ
16ኛ የዘዳዳ ቅድስት ማርያም 13 ጥማድና 18 ዶመኛ
17ኛ የጭቅማ ቅዱስ ሚካኤል 29 ጥማድና 19 ዶመኛ
18ኛ የጉር አባ ኪዳነ ምሕረት 28 ጥማድና 11 ዶመኛ

በጠቅላላ በሥራ የተሠማሩት 460 ጥማድ በሬና 234 ዶመኛ ናቸው ። እነዚህ ከ1 - ተራ ቁጥር እስከ 18 ድረስ በዝርዝር የቀረቡት አብያተ ክርስቲያናት ከየቀበሌአቸው የገበሬ ማህበር ለአትክልትና ለልዩ ልዩ የእህል ዘሮች የሚሆን ሰፊ ቦታ ተረክበን በማልማት ላይ እንገኛለን ብለዋል ።

ትንሣኤ ይህንን የእርሻን ልማት ለማቋቋም ያቀዳችሁበት ምክንያት ለምን ይጠቅማል ብላችሁ ብታምኑበት ነው?

መልስ የእርሻውን ልማት ለማልማት ያቀድንበት ዋና ፍሬ ነገር ብዙ ጉዳዮችን ይሸፍንልናል የጎደለውንም ይሞላልናል በሚል እምነት ሲሆን ከዚህም ሌላ 1ኛ የቤተ ክርስቲያንን እድገት ለማጠናከርና ለማጎልመስ 2ኛ በየዕለቱ ገንዘብ አዋጡ ብሎ ምእመናኑን ከማስቸገር ይልቅ ሁላችን ማለትም ማህበረ ካህናቱና ምእመናኑ ጉልበታችንን በሥራ አስተባብረን በቂ ገንዘብ ለማግኘት ይቻላል የሰውንም እጅ ከማየት ያድናል በሚለው መንፈሳዊ መመሪያ ነው ።

ትንሣኤ ይህ ዓይነቱን የልማት ሥራ ስትጀምሩ ያጋጠማችሁ ችግር አለወይ ?

መልስ በሥራችን ያጋጠመን አንዳችም ችግር አልነበረም

ትንሣኤ በሬ ካለ ዶመኛ ያስፈለገበት ምክንያት እንዴት እንደሆነ ቢገልጹልን

መልስ የሚዳ ወረዳ ደጋ ወይና ደጋ ቆላ በመሆኑ በተለይም የቆላው መሬት ወጣገባ ከመሆኑ የተነሣ ዶመኛው ገበሬውን እየተከተለ የቀረውን ሥራ ሥርና ቅጠላ ቅጠሉን እየነቀለ ማጥፋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው።ገበሬ ያረሰውን እንደገና ዶመኛ እየተከተለ ካላስተካከለው ጥሩ ውጤት ሊያስገኝ ባለመቻሉና እስከ ዛሬም ቢሆን የዚህ ዓይነት ሥራ የተለመደ ነው

ትንሣኤ ለመሆኑ ይህንን በልማት ያቀናችሁት መሬት እንዴት ልታገኙ ቻላችሁ ?

መልስ ማህበረ ካህናትና የገበሬ ማህበር በቤተክርስቲያን በኩል አንድ ስለሆንና በመካከላችን ልዩነት ስለሌለን በሐሳብ



www.ethiopianorthodox.org

ም ሆነ በመንፈሳዊ ሥራ ስለቤተ ክርስቲያን ያለን አስተሳሰብ አንድ በመሆናችን በእርሻው መሬት ያጋጠመን ችግር የለም

ትንሣኤ ባሁኑ ዓመት ባለማችሁት መሬት ላይ የዘራችኋቸውን የዘር ዓይነቶች ቢገልጹልን?

መልስ ለጤፍ ለስንዴና ለማሽላ ተስማሚ የሆነውን ቦታ ቀደም ብለን አርሰንና አለስልሰን ተዘጋጅተን ስለቆየን በደጋው ልማት ስንዴን በቆላው ልማታችን ደግሞ ማሽላንና ጤፍን ዘርተን እነሆ መሬት የምትሰጠውን በረከት ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ ነን ።

በመራቤቴ አውራጃ በሚዳ ወረዳ የሚገኙት ማህበረ ምእመናን ቀሳውስት ምእመናን ተብለው ባለመለያየት በመተባበርና በመግባባት ቤት ክርስቲያን የምትሻሻልበትን ዘዴ በመፍጠር በልማ ሥራ መሰመራታቸውን ከዚህ በላይ ተመልክተናል ይህንን በሚዳ ወረዳ የሚከሄደውን የእርሻ ልማት ፀመመልከትና የእነርሱን አርያያ በመከተል ሁሉም በየአካባቢው የሚገኘውን መሬት እያለማ መጠቀም ይኖርበታል እንላለን

ክንፈርግብ ማርቆስ

## የችቦና የደመራ ....

ከገጽ ፲፱ የዞረ

ገድ ደግሞ መስቀሉን ፍለጋ ይቆፍሩ የነበሩት ሰዎች ሲመሽ ከሚዳ ላይ እንጨት ደምረው እያነደዱ ምግባቸውን ይመገቡና ይሞቁ ያበሩም ስለነበር የዚህን ምሳሌም የያዘ ይመስላል ። አሁንም እነዚህ ቆፋሪዎች ጉድጓዱ ጥልቀት ስለነበረውና በጣም ጨለማ ስለሚሆንባቸው የችቦ መልክ ያለው መብራት ይዘው ስለሚገቡ የአሁኑ የችቦ ብርሃን ከዚያ ሲያያዝ የመጣ ምሳሌ ይመስላል ። በየአደባባዩና በየመንደሩ ሕዝቡ ችቦ ማቀጣጠሉ ደግሞ የክርስቶስ በመስቀል ላይ መሰቀል ለዓለሙ ሁሉ እውነተኛ የነፃነት ብርሃን እውነተኛ የደኅንነትም ብርሃን ለማስገኘቱ ምሳሌ ሲሆን ለሰው ልጆች ደኅንነት ሲል በመስቀል ላይ የተሰቀለው ራሱ ክርስቶስም የዓለም ብርሃን ለመሆኑ ታስቦ የተደረገ ምስክርነትም ነው ።

ስለዚህም ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን በበዓሉ እሌት "ብከንወግዖሙ ለኵሎሙ ፀርነ ወበሰምክ ነኀሥሮሙ ለእለቆሙ ላዕሌነ» ጠላቶቻችንን ሁሉ ባንተ እንዋጋቸዋለን የቆሙብንንም በስምህ እናጐሣቊላቸዋለን እያለች የጠላትን መጠቃት የወገንን ማጥቃት የመስቀልን መሣሪያነት ታበሥራለች የመስቀል መሣሪያነትም በዚህ ብቻ ሳይወሰን ምእመናን ክርስቲያኖች ሁሉ መስቀል በሚሳለሙበት ጊዜ መስቀል ኃይልነ መስቀል ፀውንነ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ እያሉ ያወድሱታል ። ቅጳውሎስም "ጥልን በመስቀሉ ገድሎ በርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው" ባለው እምነታቸውን ያረጋግጣሉ ። ኤፌ. ም. 2. ቁ.26 ።

እንግዲህ "እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" ባለው የወንጌል ቃል መሠረት መስቀሉ የነፍሳችንም የሥጋችንም መድኃኒት ጠላት ዲያብሎስንም ድል የምንነሳበት መሆኑን አምነን መስቀሉን ተሸክመን እንከተለው ።

## ዜና ሊቃውንት

ከገጽ ፳፱ የዞረ

"አንበሪ ዘባሕር ወዘቀላያት ፣በፀዊረ አምሳል ካዕበተ ገራህተ አብርሃም ተመሰለ።መቅደስ ሩፋኤል መልአክ እስመ በዘባኑ ሐዘለ ። ወበውስተ ከርሡ ዘዮናስ አካለ ። ወእምደብረ ሄኖክ ኢሰሰለ ። ተከለ ኀድዐቱ ለማይ እስመ በዘባኑ በ ቈለ ።

ባሕቱ በይነ ዮናስ ወእንበይነ መቅደስ ክህለ ።

ተሐውሶ ወኢተሐውሶ በኀይለ ሩፋኤል ዘተለዓለእመ አንበሪ ይትሐወስ እስመ ቤተ መቅደስ እምንህለ ።

ወእመ አንበሪ ኢይትሐወስ ዮናስ እምተሐጉለ ።

አማርኛው

የጥልቅ ባሕር አንበሪ ምሳሌን በመሸከም ሁለተኛ የአብርሃምን እርሻ መሰለ ። በሆዱ የዮናስን አካል ፣ በጀርባው የመልአኩን የሩፋኤልን መቅደስ አዝሏልና ። የውሀ ፀጥታ ተክል በጀርባው በቅሏልና ከሄሮክም ደብር አልተወገደም ።

ነገር ግን ስለዮናስና ስለቤተ መቅደስ ክፍ ባለው በሩፋኤል ኃይል መነቃነቅንም አለመነቃነቅንም ቻለ ።አንበሪ ቢነቃነቅ ቤተ መቅደስ በፈረሰ ነበር፡ አንበሪ ባይነቃነቅ ዮናስ በጠፋ ነበር።

ለሊቁ ክፍ ብሎ እንደተመለከተው ሁሉ ይኸንን የመሰሉ ብዙዎች የምርምር ቅኔዎች አሏቸው ።

አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org